
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ቤተ ክርስቲያናችን ከኢትዮጵያ ጋር ትቅደም



# የብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ




፩ኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት መጽሔት

[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት

# ሐዲስ ሕይወት

## ይህ መጽሔት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

### ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፩ኛ ዓመት ሢመተ ፓትርያርክ በዓል

### በስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ ክፍል ተዘጋጅቶ

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ፡ ም፡

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ዕለታዊ ተግባራቸውን በጽሕፈት ቤታቸው
እየተገኙ ያከናውናሉ ።

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴ ።

**የኢት/ ቤተክህነት አመራር ከፍተኛ ኃላፊት የሚመሩት ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ናቸው ።**

ብፁዕነታቸው ከሀገራችን መንፈሳዊ ትምህርት ሌላ ለከፍተኛ የቲዎሎጅ ትምህርት ኢየሩሳሌም በሚገኘው ሴንት ጆርጅ መንፈሳዊ ፤ ኮሌጅ ተልከው ፫ ዓመት ተምረው በአስተዳደርናበፋይናንስ ትምህርት ተመርቀዋል ። በእዚያም የሚሰጠውንትምህርትከፈጸሙበኋላ ወደኢትዮጵያ ተመልሰው ልዩልዩመንፈሳዊ ግልጋሎትን አበርክተዋል ።

በመንፈሳዊ ግልጋሎት መልክ ላይ ተሰማርተው ከሠሩባቸው ክፍሎች መካከል በማኅበራዊ ኑሮ ፤ የዑራል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው በመሥራትና የስብከተ ወንጌል ኃላፊ ሆነዋል በኋላም ደግሞ በከፋ ክፍለ ሀገር ጅማ ውስጥ ሊቀ ጳጳሱን በመወከል ያለ ሊቀ ጳጳስ ፳ ዓመት ሙሉ ሠርተዋል ።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ያላቸውን መንፈሳዊ አስተሳሰብና የሥራ አመራር ችሎታ በማመዛዘን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፡ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ሬቃድ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ፡ እንደራሴ ሆነው የቤተ ክህነቱን ሥራ ይመራሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ የሆኑበትየ፭ኛ ዓመት በዓል አከባበር

## ፕ ሮ ግ ራ ም ፤

፩ኛ/ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፭ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በመላው የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል ፡

፪ኛ/ ትናንት ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ለዛሬ ግንቦት ፩ ቀን አጥቢያ ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ጀምሮ ለ፳ ደቂቃ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የደወል ድምጻቸውን በማሰማት የበዓሉን ታላቅነት ገልጸዋል ። ቀጥሎም እስከ ንጋቱ ፩ ሰዓት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያንና በሌሎቹም አብያተ ክርስቲያናት የጸሎቱ ሥነ ሥርዓት ተካሒዷል ።

፫ኛ/ ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት የአዲስ አበባ አድባራት አለቆችና መምህራን ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናትና ድርብ የለበሱ መዘምራን በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በመጋቤ ካህናቱ አስተናባሪነት የተወሰነላቸውን ቦታ ይዘው ቅዱስነታቸውን በታላቅ ደስታ ተቀብለዋል ።

፬ኛ/ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትንና ጳጳሳትን አስከትለው ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ከ፲፭ ደቂቃ ከቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንደ ደረሱ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና የአድባራት አለቆች በግራና በቀኝ የተሰለፉ ካህናትና መዘምራን የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት መምህራንና ተማሪዎች በታላቅ ክብር ቅዱስነታቸውን ተቀብለዋቸዋል ።

፭ኛ/ ጸሎተ ቅዳሴው ከጧቱ በ፩ ሰዓት ተጀምሮ በ፪ ሰዓት ከ፴፭ ደቂቃ ተፈጽሟል ።

፮ኛ/ ከጸሎተ ቅዳሴው በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ከዚህ ዕለት ያደረሳቸውን አምላክ በማመስገን ለ፲ ደቂቃ ያህል መንፈሳዊ ንግግር ካደረጉ በላኋ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

ክርስቲያናችን ከኢትዮጵያ ጋር ትቅደም ።

www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# በመንፈሳዊ ጥበብ የተጌጠና ትዕግሥት ከሞያ ጋር ያስተባበረ መንፈሳዊ አባት

በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ቤተ ክርስቲያን መርጣ የሾመችው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርዕሰ
ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ።

የቅዱስነታቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ተሻግረን በመጠኑም ቢሆን ለመግለጽ
እንሞክራለን ከእዚያ በፊት በእዚህ አጋጣሚ ጊዜ በቀደምትነት ለመግለጽ የምንሻው
ነገር ይኖራል ቅዱስነታቸው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ናቸው በሚለው
አስተሳሰብ ላይ ብዙዎች ሁለተኛው በመሆናቸው ቀደምት እንዴት ይሆናሉ ? የሚል
አከራካሪ ነገር አልፎ አልፎ ይሰማል ይህ መጽሔት ስለ ቅዱስነታቸው ቀዳሚነት ትም
ህርት ሳይሰጥ አያልፍም እርግጥ ሁለተኛው ፓትርያርክ ናቸው ፤ ዳሩ ግን ለብዙ ዘመ
ናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስትመኘው የኖረችው በራሷ መንፈሳውያን አባቶች
በራሷ ቤተ ክርስቲያን ራሷ መርጣና ሾማ የምታወጣውን ፓትርያርክ ነበር ለእዚህ
ዕድል ቀደምት የሆኑት ለፓትርያርክነት ሕይወት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ
መንፈሳዊ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ በመሆን በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ሢመተ ፓትር
ያርክነት የተቀዳጁት አባ ቴዎፍሎስ ናቸው ። ከእዚህም የተነሳ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ መባል
ተገባቸው ይህም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ የሆነ መንፈሳዊ ታሪክን የጨበጠ
ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥር
ዓት መሠረት ከፍተኛውን የትምህርት ደረጃ የያዙ ሊቅ ናቸው ፤ በቅዱስነታቸው ሕይ
ወት ቤተ ክርስቲያናችንና እውነተኞች የሆኑት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተከታዮች በእ
ባትነታቸው የሚኮሩባቸው ሌላ መንገድ አለ ፤ ይኸውም በውጭ ሀገር ልዩ ልዩ ቋንቋ
ዎች የመናገርና አለአስተርጓሚ ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊውያን መሪዎች
ጋር በቀጥታ ሐሳብ ለሐሳብ የመለዋወጥ ችሎታቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን
በሥልጣኔ አንጸዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርካችን ለእዚህ ከፍተኛ የሆነ ታላቅ መንፈሳዊ ግልጋሎት ከመድረ
ሳቸው አስቀድሞ በልዩ ልዩ መንፈሳውያን ግልጋሎት ላይ ተሰማርተው ፤ የሚፈለግ
ባቸውን ተግባር ለቤተ ክርስቲያናቸውና ለኢትዮጵያ ምዕመናን አበርክተዋል ።

በመጀመሪያ መምህር መልእክቱ ተብለው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንን ገዳም
በእልቅና ቀጥሎም ሊቀ ሥልጣናት ተብለው የመጀመሪያው የቅድስት ሥላሴ ገዳም
አስተዳዳሪ ሆነዋል ፤ በእዚህ ጊዜ ለካህናቱ ዘመናዊ አመራርና ፤ የቀለጠፈ የቤተ ክርስ
ቲያን ሥነ ሥርዓትን በማስጨበጥ ሠርተዋል ።
በኋላም ለጵጵስና ደረጃ ተመርጠው የሐረር ሊቀ ጳጳስ በመሆን በሚያስተዳድሩት ክፍለ
ሀገር ዘመናዊ የሆኑ ወጣቶችን በማሰልጠን ሐረር የሚገኘውን የመኮንን መንፈሳዊ
መምህራን ማሠልጠኛን በማቋቋም ለቤተ ክርስቲያናችን ብቁዕ የሆኑ ዘመናውያንና
መንፈሳውያን ወጣቶችን በትምህርት በማነጽ ብዙ ፍሬን አስገኝተዋል ።

ቀደም ብሎም የቅድስት ሥላሴ ገዳም አስተዳዳሪ በነበሩበት ጊዜ መንፈሳዊው
ትምህርት ከሥጋዊው ዕውቀት ጋር ተዛምዶና ተዋህዶ እንዲራመድ ለማድረግ በአላ
ቸው ጥረት በእዚያን ጊዜ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እየተባለ ይጠራ
የነበረውን የዛሬውን መንፈሳዊ ኮሌጅ እዚህ ደረጃ ላይ ለማድረስ ያስቻለው የቅዱስነ
ታቸው ከፍተኛ ጥረትና ዘመናዊ አስተሳሰባቸው ነው በእዚያን ጊዜ የነበሩት ተማሮቻቸው
ለአሁኑ ጊዜ ምሥክርነታቸውን የሚሰጡ በብዛት ይገኛሉ ትምህርትን ላለመቀበል
ይደርስ የነበረውን የደካሞች አስተሳሰብ በማስተማርና በማለስለስ ትውልዱ መንፈሳ
ዊውን ትምህርት ከሥጋዊው ትምህርት ጋር አዋህዶ እንዲጠቀምበት በአደረጉት
ጥረት ዛሬ ከእዚያ ትምህርት ቤት ወደ ውጭ ሀገር ተልከው የተማሩት ብዙዎቹ በዶክ
ተርነት ደረጃ ከፍ ብለው ትምህርት ገብይተው በመመለሳቸው ፬አሁኑ ጊዜ ለሀገራቸው
የሥራ እርምጃ ተካፋይ በመሆን ከፍተኛ የሥልጣኔ እርምጃን አፍርተዋል ።

ብፁዕ ፓትርያርኩ በዘመናቸው መካከል ፍጹም የሆነ ደስታ አግኝተዋል ብለው
የሚያምኑ አልታጡም ዳሩ ግን ብዙ ችግር ብዙ ተዕዕኖ ሲፈራረቁባቸው የኖሩ ታጋሽ
አባት ለመሆናቸው በቅርቡ የቅዱስነታቸውን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያውቁ ሁሉ በግ
ልጽ ይረዳሉ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ከእዚህ ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ የበቁት በልዑል እግ
ዚአብሔር ፈቃድና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሕይወት በመታደል በመሆኑ በተራማጅነት
መንፈስ ዛሬ ኢትዮጵያ በምታካሒደው ቅዱስ ለውጥ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛውን
የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ በመደገፍ አብራ በሥራውና በለውጡ ተዋህዳ ለመራመድ ችላ
ለች ።

ጥሩ አመራርን የሚያውቅ መንፈሳዊ አባት የብዙዎች አድኃርያን ጩኸትና ዛቻ
ወደኋላ ስለማይገታው ከኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማ ጋር ወደፊት ቤተ ክርስቲያኒቱን
ከመምራት ወደ ኋላ አይልም ለብዙኀን ጥቅም ሲባል ለተጀመረው ንቅናቄያችን በተራ
ማጅነት መንፈስ ቤተ ክርስቲያናችን በምታካሔደው ለውጥ የቀድሞው ጭቆና ተባባሪ
የነበሩና ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲመዘብሩ ከነበሩት ክፍሎች በጥቅም በመሰባጠር የሚደረ
ገው ተቃውሞ በዛሬዪቱ ኅብረተ ሰብዓዊነት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ዋጋ ስለማይኖ
ረው በትዕግስት ባህርይ የሚመለከቱት ቅዱስ ፓትርያርኩ የተራማጅነት ህልውናቸውን
በግልጽ ይመሰክራል ።

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ታሪክ
ውስጥ ይህንን የመጀመሪያ ፓትርያርክነት ደረጃ በክብር የተቀዳጁበትን አምስተኛ
ዓመት በዓለ ሢመት ቤተ ክርስቲያናችን በታላቅ ሥነ ሥርዓትና በአዲስ ተራማጅነት
ታከብራለች ።

ሰፊ ትዕግሥት አመዛዛኝነትና ፈጥኖ ከማድረግ ትክክለኛ መመርመርን የሚወዱ
ፍጹም መንፈሳዊ አባት በማግኘታችን በተራማጆች ክርስቲያኖች ምዕመናን ዘንድ ተወ
ዳጅነትን ያገኙት ፓትርያርክ በኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማ ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲ
ያራምዱት እንመኝላቸዋለን ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነቴ ዎፍሎስ መንፈሳዊና ተራማጅነት አስተሳሰባቸው በብሔራዊ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነቴ ዎፍሎስ መንፈሳዊና ተራማጅነት አስተሳሰብ የተነሳ ዛሬ የዓ
ደረጃ ብቻ የማይለካ በመሆኑ ቅዱስ ፓትርያርኩ በአላቸው አስተሳሰብ የተነሳ ዛሬ የዓ
ለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ፤ የመላው አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናት ማበሕር
የክብር ፕሬዝዳንት ናቸው ።

አስተዋይነትን ከመንፈሳዊ ዕውቀት ጋር አዋህደው በሚራመዱት ፓትርያርካችን
ቤተ ክርስቲያናችን ትኮራለች ።





ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለምእመናን ቃለ ምዕዳን ሲያስተላልፉ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ለዘመን መለወጫ ያስተላለፉት

## መልእክት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የ፲፱፻፹፯ ዓ ም የዘመን መለወጫን በዓል ምክንያት በማድረግ ከዚህ የሚከተለውን ቃለ ቡራኬ ሰጥተዋል ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ። ዘኢኮነ በእንተ ሰብዕ ወኢኮነ እምኀበ ሰብዕ ዘእንበለ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወእግዚአብሔር አብ ዘአንሥኦ እሙታን ።

የቤተ ክርስቲያን መልእክትና አገልግሎት ትምህርት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ና ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ፤ በሱ ቸርነት ፤ በሱ መሪነት የሰውን ዘር ሁሉ በእኩልነት ለማገልገል ፤ ለመርዳት ፤ ለመምራት የተቋቋመ የተዘረጋ የታቀደ ነው እንጂ ከሰው መንጭቶ የሰውን አፍአዊ ፍላጎት ለማሟላት ለሰው ተብሎ ለሰው ይምሰል የሆነና የሚሆን አይደለም ።

ቤተ ክርስቲያን ማለት ራሱ የሰው ዘር ሁሉ ሕይወቱን ለማሟላት ዓላማውን ለማ ስተካከል ከኃጢአት ተለይቶ በሰላም በጽድቅ ታድሶ አሮጌ ሰውነትን ጥሎ አዲስ ሰው ነትን ለብሶ ለመኖር በእግዚአብሔር መንፈስ እየተረዳ በአንድነት የሚሠራበት አን ድነት የሚመራበት ማኅበራዊ አንድነት ማለት ነው ። የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ልዩነትን የማያሳይ ለሁሉም ነው ።

የመድኃኒታችንም ዓዋጅ ሰላም ለኵልክሙ ሰላም ለሁላችን ይሁን የሚል ነው ። ስለ ሰላም ፤ ስለፍትሕ ስለ አገርና ስለ ሕዝብ ደኅንነት በፀጥታ ስለ መኖር ዝናብ በሚ ፈለግበት ቦታ እንዲገኝ ፤ ወንዞች እስከ ልካቸውና እስከ ወሰናቸው እንዲሞሉ ፤ ከልክ እንዳያልፉ የሕዝብ ጥቅምና ሕይወት እንዳያጠፉ ፤ የምድር ፍሬ እንዲበዛ ፤ በረከት እንዲያገኝ ፤ ከዘር ተርፎ ለምግብ እንዲበቃ ፤ ድውያን ከሕመማቸው እንዲፈወሱ ፤ መንገደኞች ሁሉ በወጡበት መልካሙ ሥራቸው ተከናውኖላቸው በሰላም እንዲመለሱ ፤ መሪዎች ሥራቸውን በትክክል እንዲሠሩ ፤ ሕዝባቸውን በእኩልነት እንዲያስተዳድሩ ፤ ሕዝብና አሕዛብ በሰላም በፍቅር እንዲኖሩ ፤ ርስበርሳቸው እንዲከባበሩ ፤ እግዚአብ ሔርን እንዲፈሩ ረድኤቱን ደጅ እንዲጠኑ ፤ እሱን ብቻ በንጹሕ ልብ እንዲያምኑ ፤ ከሁሉ አስቀድማ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ፤ ከዚያም አልፋ ከጎረቤቶቿ ጋር ያለው ኑሮ የተካከለ የተደላደለ ሰላማዊ ጉርብትና ያለበት እንዲሆን ፤ መላው ዓለምም በሰላም እንዲኖር በመዓልትም በሌሊትም ያለማቋረጥ አዘውትራ ትጸልያለች አገልግሎቷንም በዚሁ ታበረክታለች ።

የዘመን መጀመሪያና መጨረሻ ስለሌለው ዘመን ተለወጠ ለማለት አይቻልም ። የማይለወጠውን ዘመንተለዋጭ የሚያደርገው የሰው ልጅ ታሪክ ነው ። ለምሳሌ ለኢት ዮጵያ የጥንቱ ከዛሬው ፤ የዛሬው ከወደፊቱ የሚለየው የቀድሞው ዘመን የአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ፤ የዛሬው የእኛ ፤ የወደፊቱ ደግሞ ወደ ፊት ኢትዮጵያ የምትወልዳቸው ኢትዮጵያውያን ዘመን በመሆኑ ነው ሦስቱ ክፍላተ ዘመን የተለያዩ ቢሆንም ፤ ባለቤቶቹ ኢትዮጵያውያን ፅኑ በሆነ በማይቆረስና በማይበጠስ መንፈስ የተያያዙ ናቸው ።

ያለፉት አባቶቻችን የኖሩት ለራሳቸው ብቻ አልነበረም ። ተግባራቸው ቅርሳቸው ለኛ ተርፎናል ። በዚሁ አንጻር እኛም የምንኖረው ለራሳችን ብቻ አይደለም ። ማንኛ



www.ethiopianorthodox.org

ውንም ሥራ ከመጀመራችን በፊት የምንሠራው ሥራ ሁሉ ከእኛ ጀምሮ እስከሚመጣው ትውልድ የሚዘረጋ መሆኑን በልቡናችን አስቀድመን ማሰብ አለብን ።
ቅድመ ልደተ ክርስቶስም ፤ ድኅረ ልደተ ክርስቶስም ፤ ክፉና ደግን መለያ ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎች ተነሥተዋል ። ነገር ግን «አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ » ጓደኛህን ፤ እንደራስህ አድርገህ ውደድ ከሚለው በአባቶቻችን በኩል ከደረሰን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የተሻለ አልተገኘም ። የኢትዮጵያውያን ምግባረ ሠናያት በሙሉ የተመሠረተው በዚህ ትእዛዝ ላይ ስለሆነ መሠረቱን እናጥብቅ ፤ የተራበን ማብላት ፤ የተጠማን ማጠጣት ፤ የታረዘን ማልበስ የታሰረን መጠየቅ የተመሠረቱት በዚሁ ትእዛዝ ላይ ነው ። ኋላም በዕለተ ደይን የይለፍ ፈቃዳቸው ይዞታ እነዚህ ናቸው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር «አማን እብለክሙ ፤ ይቀልል ይኅልፍ ገመል እንተ ስቊረተ መርፍዕ አምባዕል ይባእ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር » ባለፀጋ ሰጥቶ መጽውቶ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ይልቅ ፤ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብታልፍ ይቀላል ያለውም ፤ ችግረኛ እያለ እንግዛ ፤ እናብዛ የሚሉትን ለመገሠፅ ነው እንጂ ብልፅግናን ፈጽሞ መቃወሙ አይደለም ።

ስለዚህ ወንድሞቻችን በፍርሃተ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመንፈስና የምቾት ብልፅግና ታጥቀው እንዲሠሩ የዘወትር ጸሎታችንን አናቋርጥም ፤ እግዚአብሔርም በአርአያው የፈጠረው ሰው እንዳይጐሳቆል በማሰብ አዳምን የፈጠረው መጀመሪያ ገነትን ካዘጋጀ በኋላ ነው ።

ሆኖም ከገነት ወዲህ መበልፀግ «በሀፈገጽከ ብላዕ ኅብስተከ» በድካምህ ወጥተህ ወርደህ ላብህን ብላ ፤ ሊሠራ የማይወድ አይመገብ ፤ ባለው መሠረት እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ ወጥቶ በሐሰትና በኃይል ሌላው ከደከመበት ላይ እጅን ማሳረፍ ያላስቀመጡትን ማንሣት እግዚአብሔርን ያስቆጣል ።

የማይለወጠውን ዘመን ተለዋጭ የሚያደርገው የሰው ልጅ ታሪክ ነው ተብሏል ። በዚህ ረገድ ይህ ያለቀው ፲፱፻፷፯ ዓ/ ም የሚረሳ አይደለም ። ፲፱፻፷፯ ዓ/ ም ሰላም በይበልጥ የሰፈነበት ዘመን እንዲሆን ሁላችንም በጸሎት እንጠመድ ። ኢትዮጵያ በመርከብ ትመሰላለች ከተባለ ፤ የመርከቢቱን አቅጣጫ ለማቃናት ተሳፋሪዎቹ ሁሉ አላፊነት አለባቸውና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያላንዳች መለያየት በፍጹም ሃይማኖት ተጋግዞ ማፅናትና ወደ ቀናው መንገድ መርከቢቱን መምራት ግዴታቸው ነው የሐ/፳፯ ፲፮/፲፯ ። ለሁሉ ጥሪ ሲደረግ «እስመ ብዙኃን ፅዉዓን ወኅዳጣን ኅሩያን እንዳይሆን እያንዳንዱ ሰው ማሰብ አለበት ። ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ሰላም የሰፈነበት እንዲሆን በጸሎት እንጠመድ ፤ ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የአንድ እናት የኢትዮጵያ ልጆች በይበልጥ የሚተሳሰቡበት፤ የሚተሣሠሩበት ፤ ተዋሕዶአቸውን የሚያጠነክሩበት የአዲስ ዘመን መጀመሪያ እንዲሆን ምኞታችንን በሥራ እናሳይ ።

ማንኛውም ሰላማዊ ኢትዮጵያዊ ማኅበርም ሆነ በግል የጉዳዩ ባለቤት እሱ ራሱ ስለሆነ ያላንዳች ፍርሃትና መገላመጥ ጉዳዩን እየፈጸመ በሰላም በደስታ ፤ በፀጥታ በእምነት የሚኖርበት ሥርዓት እንዲኖር ሁላችንም ድምፃችንን ወደፈጣሪያችን ከፍ አድርገን እንጸልይ «ኢተሀበኒ ብዕለ ወንዴተ አላ ዘየአክል ሥራዕ ሊተ» እጅግም ሀብታም አታድርገኝ ፤ እጅግም ደሀ አታድርገኝ ፤ የሚበቃኝን አዘጋጅልኝ እንጂ። የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ጸሎት ጸሎታችን ይሁን ።



www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቤተ ሰቦች ስለሆንን አንዱ አባል ለሕዝቡ ፤ ሕዝቡ ለአንዱ አባል ያላቸው መተሳሰብ የአንድ ቤተ ሰብ መተሳሰብ እንደሆን የዘወትር ጸሎታችን ይሁን ።

ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ በእናታቸው ቤት ሲኖሩ እነሱነታቸው በማኅበራቸውና በብቸኛነታቸው ተመጥኖ ሙገለጥ የመንፈስ ደስታ ምንጭ መሆኑን እንወቅ ።
አዲሱ ዘመን ለመልካም ሥራ የተባረከ እንዲሆን ፤ ሥራችንም አንድነት ፤ ፍቅር ሰላም ፤ ዕድገት ብልፅግና ለሰው ዘር የሚጠቅመው ሁሉ የሚገኝበት የተባረከ እንዲሆን ፤ አገራችንን መላውን ሕዝብ እንዲጠብቅልን ልዑል እግዚአብሔርን እንለምነዋለን ። ለአስተዳደርና ለዳኝነት ለተሠየሙ ሰዎች ትክክለኛውን መንገድ እንዲገልጥላቸው ልዑል እግዚአብሔርን በጸሎታችን መላልሰን እንለምነው ፤

በጦር ኃይሉና በሕዝቡ የተጀመረው የተቀደሰ እንቅስቃሴ መልካም ውጤት እንዲያስገኝ ፈጣሪያችን ይርዳን ። ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘርጋ ።
ኢትዮጵያ ትቅደም

## ቅዱስ ፓትርያርኩ ስለዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ዓላማ ያስተላለፉት መልእክት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ «ኢትዮጵያ ትቅደም» በሚለው ዓላማ መሠረት ቤተ ክርስቲያን የዕድገትና ልማት ተባባሪ መሆኗን ወደ መንበረ ፓትርያርኩ መጥተው ለነበሩት ለጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ልዑካን ያደረጉት ገለጻ ።

ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ከቀትር በፊት የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ልኡካን በመንበረ ፓትርያርክ ተገኝተው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጋር ስለዕድገትና ልማት በኅብረት ዓላማ የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት ባሉበት በሰፊው ተነጋግረዋል ።

የንግግሩ ዋና ዓላማ ከላይ የተገለጸው ዓቢይ ጉዳይ ሆኖ ቤተ ክርስቲያን የጊዜውን ፈጣን ርምጃና እንቅስቃሴ ተከትላ ድርሻዋን የምትፈጽመው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር የሚታወቅና የሚጨበጥ አካል ያለው የአንድነት ሕይወት እንዲኖራትና ሕዝቡንም ወደ ሥራ ዓለም እንዲያመራ በከፍተኛ መንፈስ መምራት የሚገባት መሆኑን የሚያመለክት ዝርዝር ሲሆን፤ቅ/ፓትርያርኩ ቤተ ክርስቲያናችን ዕንቅስቃሴውንና ለውጡን በዓይነ ልቡና አተኩራ እያየች በታላቅ ናፍቆት ስትጠባበቀው የነበረው ነው እግዚአብሔር የሕሊና ጸሎትዋንና ልመናዋን ሰምቶ ይህን ተአምር ሲያደርግላት ለሕዝቡ ይበጃልና ይጠቅማል ተብሎ በታለመው የኅብረት ዓላማ ሁሉ ቀድማ የማትገኝበት ምክንያት የለም ብለዋል ።

ጥንቱንም ቢሆን በሐዋርያት ጊዜ እንደነበረው ማኅበር የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ተግባርና ዓላማ በሕዝብ መካከል ችግረኛ እንዳይኖር አንዱ አግኝቶ ሲበላ ሌላው አጥቶ ጦሙን እንዳያድር ያለው ከሌለው ጋር ተካፍሎ እንዲመገብና ሥጋ በለበሰው ፍጡር መካከል የተፈጥሮ ልዩነት እንደሌለ ሁሉ የኑሮ ልዩነት እንዳይኖርየእኩልነትን መንፈስ ማስተማር ነው ።

ስለ ሥራም ቢሆን ሐዋርያው ቅዱስ ፡ ውሎስ «የማይሠራ አይብላ» ያለውን ቃል
ተከትላ ስንፍናን በማውገዝ «በፊትህ ወዝ ጥረህና ግረህ ብላ» የሚለውን አምላካዊ
ዓዋጅ በትምህርት መገናኛ መሥመር ስታስተላልፍ የኖረች እንጂ በሰነፎች ፍልስፍና
ተወናብዳ ሳይሠሩ ማግኘትን ሳይደክሙ ዕረፍትን ያወጀበት ጊዜ የለም ።

ስለአንድነትና ወንድማማችነትም ቢሆን ቤተ ክርስቲያናችን የሰላምና የፍቅር መል
እክተኛ እንደመሆንዋ በአርአያ እግዚአብሔር በተፈጠረ ሰብአዊ ፍጡር መካከል የል
ዩነት አስተያየት የሰነዘረችበት ጊዜ እንደሌለ ሁሉ አሁንም ጥላቻንና ልዩነትን አስወ
ግዳ ፍጹም ሰላምና አንድነትን ለመመሥረት ከምታደርገው ጥረት የምትቆጠብበት
ምክንያትና የምታቋርጥበት ጊዜ የለም፤ በማለትቅዱስፓትርያርኩመግለጫሰጥተዋል ።

ኢትዮጵያ ትቅደም

## ስለመስቀልበዓልቅዱስፓትርያርኩያስተላለፉትመልእክት

ሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት በየሀገረ ስብከታቸው ይህንኑ የተቀደሰ ዓላማ ከማስቀደም
ወደ ኋላ የሚሉበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ብፁዕነታቸው ጨምረው አረጋግጠዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የመስቀልን በዓል ምክ
ንያት በማድረግ በአስተላለፉት ቃለ ቡራኬ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከአለባት
ኃላፊነት ጋር የኢትዮጵያውንን አእምሮ በትምህርት በማነጽ ስላደረገችው ከፍተኛ ጥረ
ትና ስላስገኘችውም ፍሬ በሀገሪቱም ውስጥ ከመንግሥቱ ይልቅ ቤተ ክርስቲያኒቱ በብ
ዛት ትምህርት ቤቶችን ለማቋቋም መቻሏን በመግለጽ ለመላው ሕዝብ ያስተላለፉት
መልእክት ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፤ የሰላማችን ምልክት
መስቀል ነው ፤ መስቀል ብለን ስሙን ስንጠራ ምልክቱንም ስናይ ታላላቅ ነገሮች ትዝ
ሊሉን ይገባል ። ከነዚህም አንዱ የኃያሉ እግዚአብሔር ፤ ፍቅር ነው ፤ ፍቅሩንም የገ
ለጸው በመስቀል ነው ፤ ይህ መስቀል በጎልጎታ ከመገኘቱ በፊት ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ
በሦስት መቶ አሥራ ሁለት ዓ ም በፈረንሣይ አገር ከሠራዊቱ ጋራ በፈረስ
ተቀምጦ ሲጓዝ በፀሐይ ፊት ለፊት የብርሃን መስቀል በሠሌዳ ብርሃን ተቀርጾ በፊቱም
በዚህ ምልክት ድል ትነሣለህ የሚል ጽሑፍ አየ ፤ በዚህ መነሻነት ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ
የክርስትናን እምነት ተቀበለ ፤ ቀጥሎም ይህንን ትምህርተ መስቀል የሠራዊቱ ምል
ክት አድርጎ ጠላቶቹን ድል ስለነሣ ፤ ስለዚህ ትምህርተ መስቀል የሃይማኖት ምልክት
የድል ምልክት ፤ የሰላም ምልክት ሆነ ፤ በሀገራችን በኢትዮጵያ የሠራዊት በዓል ከመሆን
አልፎ የሕዝብ በዓል ለመሆን በቃ ።

ምእመናን ሆይ ፤ ይህ ስም ክቡር ነው ፤ በውስጡ የእግዚአብሔርንና የልጁን
ጥልቅ ፍቅር ፤ በዚህ ፍቅርም መሠረትነት ስለኛ ሕይወት የተፈጸመውን ግብር የምናይ
በት ይህ ምልክት የማይመረመር ምሥጢር ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም የተመሠረተችው መሥራችዋ ክርስቶስ «ሑሩ
ወመሀሩ ኵሎ አሕዛበ ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ
ቅዱስ ወመሀርዎሙ ይዕቀቡ ኵሉ ዘአዘዝኩክሙ ወናሁ አነ እሄሉ ምስሌክሙ በኵሉ
መዋዕል እስከ ኅልቀተ ዓለም» ። ሂዱና ሰዎችን ሁሉ አስተምሩ ያዘዝኳችሁንአፍቅሮተ
ቢጽን ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ አስተምሯቸው እነሆ እኔ በዘመኑ ሁሉ እስከ ዓለም መጨ
ረሻ ድረስ ከናንተ ጋራ አለሁ ሲል በአስተማረው ትምህርትና በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው ።

ይህንንም ትእዛዝ በመቀበል ፤ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ረኀብ ጥም ፤ ቍር ፤
ዋዕይ ሳይመልሳቸው በእግራቸው ሊሄዱበት እስከሚችሉበት ድረስ እየሄዱ «ሂዱ አስ



ተምሩ ፡ » የሚለ ውን ትእዛዝ ፈጽመዋል ፤ ለዚህም ምስክሩ በመላ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝቡን
መስለው ከሕዝቡ መካከል የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ። እነዚህም
አብያተ ክርስቲያናትና በውስጣቸው የሚያገለግሉ ካህናት አንዳችም የመንግሥት
ድርጅት በማይገኝበት ቦታ ሁሉ ይገኛሉ ።

ቤተ ክርስቲያን በተጣለባት ፤ ኃላፊነት መሠረት የኢትዮጵያውያንን መንፈስ
በትእዛዛተ እግዚአብሔር በማርካት ብቻ አልተወሰነችም ።

ዘመን የታሪክና የሐሳብ ማከማቻ በመሆኑ ትውልድ ከትውልድ የሚወርሰው ቅር
ስና ሐሳብ በየጊዜው እየጨመረ ይሄዳል ፤ ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለባት
ኃላፊነት ክርስትናን ማብሠር ሆኖ ሳለ ፤ አእምሮ ማነጽን ተጨማሪ ኃላፊነቷ አድርጋ
ትምህርት ቤትም ሆነች ። የኢትዮጵያን ልጆች አእምሮ በትምህርት ለማነጽና ኢትዮ
ጵያን ትምህርት የተስፋፋበት አገር ለማድረግ አድባራቷንና ገዳማቷን በጠቅላላው
አብያተ ክርስቲያናቷን ሁሉ የጸሎትና የትምህርት ቤት አደረገቻቸው ፤ መንግሥት
ባለው አቅም ሁሉ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያህል በኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርት
ቤቶችን ለማስፋፋት አልቻለም ነበር ፤ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ቤተ ክርስቲ
ያናችን የሕዝቧ ሆና በሕዝብ ደረጃ የምትተዳደር ብሔራዊት በመሆኗ ነው ።

ወንድሞቼ ካህናት ፤

በዚሁ ሐሳብ እየጨመረ መሄድ ምክንያት የቤተ ክርስቲያናችን ኃላፊነት በነዚሁ
ተወስኖ መቅረት ያለበት ሆኖ አልተገኘም ፤ ሰው ፍጹም የሚሆነው የመንፈስ፤የአእምሮ ፤
የአካል እድገቱ ሲመጣጠን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህ ሦስቱ የሰው መሠረታት
የጠነከሩ ሆነው እንዲገኙ በግብርም በጸሎትም መጣር ይኖርባታል ፤

ይህ ከባድና ቅዱስ ኃላፊነት ወደምድራዊ ባለሥልጣኖች እንዲዘምት ብንጥርም
ቅድስናውን የሚያገኘው መንሥኤው በመላ ኢትዮጵያ ከተዘረጉት ከያንዳንዳቸው
አብያተ ክርስቲያናትናመቅደስ ውስጥሲሆን ነው ፤ መዝጊያዎቹ ሁሉ ያልተዘጉ የአየር
መንኰራኵር በአየር ላይ መንሳፈፍ እንደማይችል ሁሉ ከመንፈስ ፤ ከአእምሮ ፤ ከአካል
እድገት አንዱ የተጓደለበት ሰው ፍጹም ሰው ሊሆን አይችልም ፤ መንፈሱን በእግዚአ
ብሔር ተአምኖ ያላጽናና አእምሮውን ለማመዛዘን በሚበቃው ዕውቀት ያላነጸ — ሰው
ነቱን ከችግር የሚከላከልበትን ያህል ንብረት ያላበጀ በድቡሽት ላይ እንደተሠራው
ቤት የሚመስል ሰው ነው ፤ መንፌስን የሚያሽብር ነፋስ ያሠጋዋል ፤ አእምሮውን የባዶ
ቃላት ዝናም ያናጋዋል ፤ ችግርም ያለጊዜው ወደመቃብር ይገፈትረዋል ወይም ከው
ርደት ጥላ ሥር ይጥለዋል ። ስለዚህ እያንዳንዱ ካህን እያንዳንዱ ን የሚያገለግለውን ኢት
ዮጵያዊ ፍጹም ለማድረግ ያለበትን ኃላፊነት ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል ።

ምእመናን ሆይ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ወመንግሥትኒ ዘበበይናቲሃ ትትናፈቅ
ኢትቀውም ይእቲ መንግሥት ። ወእመኒ ቤት ተናፈቀት በበይናቲሃ ኢትቀውም
ይእቲ መንግሥት » መንግሥት ርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግሥትልትቆም አት
ችልም ፤ ቤትም ርስ በርሱ ከተለያየ ቤት ሊቆም አይችልም ብሎ ስላስተማረን የኢ
ትዮጵያ ሕዝብ በምንም ዓይነት ምክንያት የማይለያይ ተባብሮ መሥራት ያለበት በአ
ንድ ሰው አካል የሚመስል መሆኑን የነገራችን ሁሉ መነሻ እናድርግ ። መላ ሰውነት
ለሚፈልገው ጉዳይ ራስ የሚያስተላልፈውን የማስተባበር ትእዛዝ አንዱ የአካል ክፍል



www.ethiopianorthodox.org

አልታዘዝ ካለ ሰውነት በሞላ ይጎዳል ። ራስም በበኩሉ በአንዱ የአካል ክፍል ላይ ብቻ ካተኮረ ሰውነቱ አይጠቅምም ።

የሰላም ንጉሥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕፀ መስቀል ላይ መሞቱ የሰውን ልጅ ለማዳን ብቻ ሳይሆን የራስን ሕይወት ስለሌላ አሳልፎ መስጠትን ጭምር ለማስተማር ነው ፤ ርስ በርሳችን ከተሳሰብን ያንዱን መብት ሌላው ካልተላለፈ አንዳንድ ፈላስፋዎች እንደሚሉት «መንግሥት አልባ ኅብረተ ሰብ እስከሚቋቋም ባይደረስም ራስን ለሌላ አሳልፎ እስከመስጠት የሚያደርስ ሁኔታ አይፈጠርም ፤ የአንድ እናት ኢትዮጵያ ቤተሰብነት ስሜት ካደረብን አንዱ ሌላውን አይበድለውም ፤ ይኸንንም ጌታ በምሳሌው «መኑ ውእቱ እምኔክሙ ዘይስእል ወልዱ ኅብስተ ወዕብነ ይሁቦ ፤ ወእመኒ ዓሣ ስአሎ አርዌ ምድርኑ ይሁቦ» ከናንተ ወገን ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ማን ነው ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን» ፤ ሲል አስተምሮናል ።

ኅብረተ ሰቡ ውስጥ በደል የሚደርሰው የኅብረተ ሰቡ ሥነ ሥርዓት የቤተ ሰብን ሥነ ሥርዓት አልመስል ሲል ነው ፤ ለኢትዮጵያ ከሌላ የመጣ ሳይሆን በመጠኗና በፍላጎቷ የተሠራ ሥርዓት ለማውጣት ሁላችንም እንትጋ ።

ጥረቱም በበለጠ ፍሬ እንዲያፈራ በያለንበት ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንጸልይ እያንዳንዱ ለአቅመ ውክልና የደረሰ ኢትዮጵያዋዊ የሚፈልገውን ሥርዓት እስካልተናገረ ድረስ የሚቋቋመው የአስተዳደር ሥርዓት በምንም ዓይነት ኢትዮጵያዊ ስለማይባል ዘላቂ አስተዳደርን ለማቋቋም ያለው ዘመቻ መላ ኢትዮጵያን የሚያሰልፍ እንጂ እንደሌሎቹ ዘመቻዎች ለወታደር ብቻ የሚተው አይደለም ።

ጸጥታና ርጋታ በሌለበት ጊዜ በጽሞና ለማሰብ ስለማይቻል ሁለተኛም ካሁን በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ዓይነቱን ሥርዓተ መንግሥት የማቋቋም ልምድ ስለሌለው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የማወቅ ፤ የማስተዋል ፤ የማማረጥ የማሰብ ሱባዔ ያስፈልገዋል ፤ ሆኖም ለአሁኑ የአስተዳደር ዘመን በዚህ ምክንያት መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማዘጋጀት የማስተማር ግዳጃችንን በያለንበት እንፈጽም ፤ ጸሎታችንንም አናቋርጥ ።

ለኢትዮጵያ የሚበጃትን ለመሥራት እንትጋ ፤ ኑሯታችንም እኛ በሠራነው እኛ ባስገኘነው ይሁን ፤ የኛነታችን መግለጫ የሆነውን ባህላችንን እንጠብቅ ፤ መጥፎ ባህል ጎረቤቶቻችንን የቱን ያህል እንዳፈረሳቸው ለማስገንዘብ ፈረንሳይ የማኅበራዊ ኑሮ ፈላስፋ ጀን ጀክ ሩሶ እንደ ኤ አ በ፲፯፻፷፫ ዓ ም «አንድ አፍሪካዊ ሹም ብሆን የአገሬን ምድር የሚረግጠውን የመጀመሪያውን አውሮፓዊና ከአገሩ የሚወጣውን የመጀመሪያውን ብሔራዊ ዜጋየማንጠለጥልበትመስቀያ፤ከአገሬ ድምበር ላይ መትከሌን አስታውቅ ነበር» እስከማለት እንደደረሰ እናስተውል ።

የሀገራችን ማኅበራዊ ኑሮ በፍቅርና በኅብረት የታነፀ እንዲሆን ለችግረኞች የዕለት ምግብን ፤ ለተጨነቁት ሁሉ ዕረፍትን ይሰጥ ዘንድ ዘወትር በጸሎት እንለምነዋለን ፤ የማኅበራዊ ኑሮአችን ፅኑ መሠረት የሆነው ትክክለኛ ፍርድን ፤ ርስ በርሳችን መታዘዝንና መረዳዳትን ገንዘብ ፤ እናድርግ ፤ አምላካችን በለጋስነት ለአገራችን የሰጣትን የአፈር ፤ የድንጋይ የማዕድናት የውሃና የዕፅዋት ፤ የእንስሳት ሀብት ዘመን በወለዳቸውና ሥነ ፍጥረት ባስገኛቸው መሣሪያዎችና ዘዴዎች ለምተው ሕዝቡ ሁሉ የተሟላ ምግብ ፤ በቂ ልብስ የተስማማ ጤናና የትምህርት አገልግሎት አግኝቶ



www.ethiopianorthodox.org

በደስታ ይኖር ዘንድ በሃይማኖት ወደፀጋው ዙፋን እንቅረብ ፤ ኢትዮጵያ ለሥራም ሆነ ለጸሎት እጅዋን ትዘርጋ ።

አገራችንን በሰማያውያንና በምድራውያን በረከት ይባርክ ።

## በፓትርያርኩ ለተሰየመው የአመራር ጉባኤ በኃላፊነት ለተመረጡት ሰዎች የተሰጠ መምሪያ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የቤተ ክርስቲያን አመራር ጉባኤን በመሰየም ለዚሁ ተግባር ኃላፊነት ይሠራሉ ተብለው ለተመረጡት የተሰጠ መግለጫ ።

የሰው ልጅ በዘመናት መካከል የገጠመውን ከባድ ችግርና ፈተና ሁሉ ሲወጣው የቆየው በእግዚአብሔር ኃይልና በራሱ ትክክለኛ ጥረት መሆኑን የኑሮ ታሪኩ ይመሰክራል ። እኛ ኢትዮጵያውያንም በየጊዜው የገጠመንን ችግር ስንወጣው የቆየነው በፈጣሪ ርዳታና በራሳችንም ጥረት መሆኑን ታሪካችን ምስክር ስለሆነ ፤ ያለፈውን አብነት አድርገ ባለንበት በአሁኑም ጊዜ የሚገጥመንን ችግር በእግዚአብሔር ኃይልና በንጹሕ ሕሊና እየተመራን አገራችን ወደ ምትፈልገው ግብ በተቻለ ፍጥነት ትደርስ ዘንድ በየ አቅጣጫችን ፤ የሥራ ድርሻችንን አከናውኖ መገኘት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አለብን ።

በመሸጋገሪያ ዘመን ላይ ያለች አገር ብዙ ችግርና ፈተና ይገጥማታል ። ይሁን እንጂ ልጆቿ ከተባበሩና በፍጹም እምነት ለጋራ ዓላማና ብልጽግና በፍጹም የወንድማማችነት ፍቅር ተሣሥረው ለሥራ ከተነሡ ችግሩን በቀላሉ ለመወጣት ይችላሉ ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ፤ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናት መካከል ከዘወትር ጸሎት ጋራ አስፈላጊውን አገልግሎት ከመስጠት የተቆጠበችበት ጊዜ ላለመኖሩ ተገልጋዩ ሕዝብ ራሱ ምስክር ነው ። ከዚህም በላይ በጥንቃቄ ልናስታውሰው የሚገባን አንዳንድ የተሳሳቱ የውጭ አገር ጸሐፊዎች የቤተ ክርስቲያናችንን ፤ ያለፈ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳልነበረ በመቁጠር የኢትዮጵያን የሥልጣኔ ርምጃ ተቃዋሚ አድርገው የኢትዮጵያን አድንድነት ለማናጋት እንዲመቻቸው የጻፏቸውን ጽሑፎች መሠረት በማድረግ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተሳሳተ አስተሳሰብ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች መኖራቸውን ነው ። እነዚህ ሰዎች የተሳሳተ አስተሳሰባቸውን አርመው ቤተ ክርስቲያኗ ለተጀመረው መሻሻል ልትሰጥ የምትችለውንና ባለፈውም ጊዜ የፈጸመችው ን አገልግሎት ማስረዳት ይህ ጉባኤ ከተግባሮቹ አንዱ ያደርገዋል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱ ተጠብቆ ወደ ተደላደለ ኑሮ እንዲመራ የዘወትር ጸሎቷ ከመሆኑም በላይ የልማቱ ተካፋይ በመሆን በሥርዋ የልማትን ጉዳይ የሚያከናውን አንድ የልማት ኮሚሽን አቋቁማ የጊዜው አቋምና አቅሟ በፈቀደላት መሠረት ስትሠራ ቆይታለች ። አሁንም ቢሆን ሕዝቡ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ በተቻላት መጠን የጥረቱ ተካፋይ ከመሆን አትቆጠብም ።

ባሁኑ ጊዜ መንግሥት ኢትዮጵያ ትቅደም በሚል ዓላማ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብልጽግና በሚያደርገው ጥረት ቤተ ክርስቲያን ከፍ ተኛ ድርሻ እንዳላት የታወቀ ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በማስተማር በኢትዮጵያ ትቅደም ዓላማ ኢትዮጵ

ያን ለማስቀደም ፤ መጣር ተግባርዋ እንደሆነ ታውቃለች ። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ተግ
ባር በሙሉ ኃይሏ ተሳታፊ እንድትሆን በመጀመሪያ ደረጃ የራሷን አቅዋም ፤ መብትና
ግዴታ ዋን መመርመርና ማስተካከል ልትፈጽመው የሚገባ ርምጃዋ ነው ።

ይህንን በመገንዘብ ከየክፍሉ የተውጣጡ ካህናትና ምእመናን አባሎች የሚገኙ
በት አንድ ጉባኤ መሰየም እንደሚያስፈልግ ቅዱስ ሲኖዶስ ስላመነበት ይህ የቤተ ክር
ስቲያንን የወደፊት ርምጃ እያጠና በሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚፈልግ ጉባኤ
እንዲቋቋም ተደረገ ዛሬ የሩጫና የጥድፊያ ጊዜ በመሆኑ ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች
ጐን ሆኖ ችግራቸውን እንዲያቃልል ይህ ጉባኤ ተመሥርቷል ። ይህ ጉባኤ የቤተ ክር
ስቲያንን ጠቅላላ አቅዋም መርምሮና አቀናብሮ የሚያቀርብ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን ፤

- መብትና ግዴታዋ ተለይቶ የምትመራበትን አስተዳደር ፤
- ምእመናን በአስተዳደሩ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ
- ከመንግሥት ጋራ የሚኖራትን ግንኙነት ፤
- በልማት ረገድ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን (ሰበካ) የራሱን ት/ቤትና የልማት ድርጅቶች የሚስፋፉበትን ፤ ካህናቱ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትንና የሚተዳደሩበትን ፤

ሁሉንም መሥራት የሚቻለው በገንዘብ ኃይል በመሆኑ ያላት ሀብትና ንብረት
ተለይቶ የሚታወቅ በትንና የሚጠበቅበትን መንገድ በሰፊው ከሚያጠናቸውና ዓበይት
ጉዳዮች ዋናዎቹ ናቸው ።

እዚህ ላይ ለማስታወስ የምንወደው ፤ ለዚህ ከፍተኛ ጉባኤ አባል ሆነው የተመረ
ጡት ስለቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸው ባላቸው ፍቅርና ኃላፊነት ጊዜያቸውንና ጉል
በታቸውን መሥዋዕት ለማድረግ የተመረጡ መሆናቸውን ነው ። ይህም በነዚህ አባሎች
የተወሰደው በጎ ፈቃደኝነት ማንኛውም ለቤተክርስቲያኗ ርምጃ ተቆርቋሪ የሆነ ሁሉ
ሊፈጽመው የሚገባ ለመሆኑ ተቀዳሚ ምሳሌ ነው ።

በዚሁ አንጻር ለጉባኤው አባሎች ልናስታውሳቸው የሚገባ ጉዳይ አለ ፤ የዚህ ጉባኤ
ተግባር ከፍተኛና ኃላፊነት ስላለበት በጥንቃቄና በማስተዋል መሥራት እንደሚያስፈ
ልግ ነው ። ከዚህም በላይ በዚህ በመሸጋገሪያ ዘመን ይህን ዐቢይ ተግባር ለማከናወን
ከፍተኛ መሥዋዕትነትና ራስን ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት አሳልፎ መስጠት ከክርስቲ
ያን የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑ መታወቅ አለበት ።

ስለዚህ ፤ ይህን የተቀደሰ ዓላማ ለመመርመርና ተገቢ መልስ ለመስጠት በበጎ ፈቃ
ደኝነት ስትሰለፉ የበጎ ነገር ምንጭ የሆነው የምታገለግሉት ልዑል እግዚአብሔር እን
ዲመራችሁ እንጸልያለን ።

እግዚአብሔር የኢትዮጵያን እርምጃ ይባርክ ።

## ቅዱስ ፓትርያርኩ በተፈጥሮ አደጋ በሀገር ውስጥ ስለደረሰው ችግር ምህላ እንዲያዝ ያስተላለፉት መልእክት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ
በኢትዮጵያ ላይ በተፈጥሮ አደጋ ድርቅ ለአጠቃቸው ሀገሮች ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፷፯
ዓ/ም ጀምሮ በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙት ገዳማት ፡ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲ
ያናት ሦስቱን ሱባኤ መላ ምእመናን ልባዊ ጸሎት እንዲያደርጉ ያስተላለፉ ቃለ በረከት ።

ቤ/ክ/ ለዕውቀትና የሥራ ዘመቻ መርሀ ግብር በሚገባ የምትተባበር መሆኗንትዱ
ስነታቸው ገልጸዋል ።

የቅዱስነታቸው ሙሉ መልእክት ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

የመላዋ ኢትዮጵያ ምእመናን ሆይ ! ፤

በዚህች ዕለትና ሰዓት ልዑል እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ቃለ ምዕዳን (የም
ክር ቃል) እናሰማችኋለን ።

### የምናሰማችሁም ቃለ ምዕዳን ፤

፩ኛ/ ስለ ጸሎት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ፤
፪ኛ/ በእድገት በኅብረት የሥራና የእውቀት ዘመቻ ቤተ ክርስቲያን ስለምትካ
ፈልበት ሁኔታ ፤

፫ኛ/ በድርቅ ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ወገኖቻችን በገንዘብም ሆነ በጉ
ልበት ቤተ ክርስቲያን በምንና በምን መርዳት እንደምትችል ነው ።

፩ኛ/ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ሀገር ሰላም ፡ ስለ ሕዝቧ ደኅንነት ከመጸለይ ያቋ
ረጠችበት ጊዜ የለም ፤ ቀሳውትና ዲያቆናት ፡ ካህናት ሌሊት በጸሎተ ሰዓታትና በማ
ኅሌት ፡ በነግህና በሠርክ ፡ በጸሎተ ነግህና በጸሎተ ሠርክ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ
ለአገርና ለሕዝብ ምሕረትን ፡ በረከትን መለመን የዘወትር ሥራቸው ነው ።

አሁንም ቢሆን በካህናቱ በኩል በገዳማትና በአድባራት በገጠር አብያተ ክርስቲ
ያናት ከዚህ በላይ የተገለጸው ጸሎት ያልተቋረጠ ነው ። እግዚአብሔር አምላካችን
በችግራችን ሁሉ ወደርሱ እንድንጮኽ «ወደኔ ጩህ እመልስልሃለሁ» ብሏል ። ትንቢተ
ኤርምያስ ምዕ ፴፫ ቊጥር ፫ ።

በማይታበል አምላካዊ ቃሉ ሲያረጋግጥልን «በሃይማኖት ፡ በነገድ ልዩነት ሳን
ፈጥር ተባብረን ወደ ፈጣሪያችን አንጮህም? ዛሬ ወደ አምላካችን ያላመለከትን ፈጥ
ነህ ድረስ ብለን በአንድነት ያልጠራነው መቼ ልንጠራው ነው ።

ሁላችሁም እንደምታውቁት በወሎና በትግሬ የጀመረው ድርቅ እነሆ የኢትዮጵ
ያን የሀገር ክፍሎች በማዳረስ ላይ መሆኑን ሁላችንም ሰምተናል። ይህን የመሰለ ፈተና
ሊወገድ የሚችለው ሁሉን የሚችል አምላካችን የምሕረት ዓይኑን ወደ አገራችንና ወደ
ሕዝባችን መለስ ሲያደርግ ብቻ ነው ። መድኃኒታችን ከኃጢአት ነጻ ሊያወጣን በተገ
ለጸ ጊዜ «ለምኑ ይሰጣችኋል ፡ ፈልጉ ታገኛላችሁ ፡ በር ምቱ ይከፈትላችኋል የሚለምን
ሁሉ ይቀበላል ፡ የሚፈልገውም ያገኛል በር ለሚመታም ይከፈትለታል ። ማቴ ም ፯
ቊ ፯—፱) አስተምሮናልና ፡ ቸርነቱ ንም ገልጾልናል ።

በድርቅ ምክንያት ምድራችን የተገፈፈችውን የልምላሜ ጸጋ በእግዚአብሔር ይቅ
ርታና ቸርነት እንድትጎናጸፍ ፡ ያጣው የተቸገረው እንዲያገኝ ፈጣሪውን በኅብረት በም
ህላ ጸሎት መጠየቅ የ ፍጡራን ሁሉ ግዴታ ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያን ጊዜ አብረውት ለነበሩት «እስካሁን በስሜ
ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ» ብሏል
ዮሐ ፲፮ ፳፬ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትናንትና የዛሬና የነገ የዘለዓለምም ጌታ ነው ፡ በዚያን
ጊዜ የተናገረው ቃል ለዘለዓለም ሲሠራ ይኖራል ። ምናልባት በአገራችን በደረሰው



www.ethiopianorthodox.org

የድርቅ ችግር ምክንያት እስካሁን እያንዳንዱ በግልም ሆነ በማኅበር የማይጸልይ አይገኝም ፤ የአገራችንና የሕዝባችን ኀዘንና ችግር ወደ ደስታ እንዲለወጥ ስንሻ ከልብ መጸለይና ምህላ ማድረግ ጊዜው አሁን ነውና በግልና በቤተ ሰብእ ፤ በማኅበራዊ ጸሎት ፈጣሪያችንን እንማጸነው ። በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መጻሕፍትም ሁሉ ፍላጎታችንን በጸሎት መግለጽ እንደሚገባ ፤ እሱም ጸሎታችንን ቸል እንደማይል ያስረዱናል ፤ ኢሳይያስ «ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ » ብሏል ። ኢሳ ምዕ ፷፭ ቍ ፳፬ ።

ምሕረት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላካችን ጸሎታችን ከልብ ሆኖ እንደፈቃድህና እንደ ቸርነትህ ይደረግልን ይፈጸምልን ካልን ጠለረድኤቱን ያወርድልናል እክለ በረከትንም ይሰጠናል ። በሕይወትም ይጠብቀናል ።

ልብና አፍ ተባብረው በእምነት ጸንተው ታላቁን የምሕረት አባት ፈጣሪ ካልለመኑት መልሱ ይዘገያል ። መልስ በቶሎ ማግኘት የምንችለው ግን አፋችንንና ልባችንን አስተባብረን ፤ ርስ በርሳችንም በፍቅር አንድ ሆነን ስንጸልይ ብቻ ነው ።

ስለዚህ ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ጀምሮ ሦስቱን ሱባኤ በመላዋ ኢትዮጵያ የሚገኙ ገዳማት ፤ አድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በጠቅላላው ጧትጧት ጸሎተ ምህላ ከልብ እንዲያደርሱ በዚህ ጸሎት ወንዶችና ሴቶች ምእመናን ፤ ወጣቶችም ጭምር እንዲተባበሩና ከልብ እንዲጸልዩ አደራ እንላቸዋለን ። ይህንም መንፈሳዊ ቃል የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት በደብዳቤ እንዳያስተላልፉ እናሳስባቸዋለን ። የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ካህናት ሰባክያንና መምህራን በዚህ ታላቅ መንፈሳዊ ሥራ ተባባሪዎች ሆነው የጸሎቱን ተግባር እንዲያስፈጽሙ አደራችን የጠበቀ ነው ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ የረኃብ ቸነፈር ሲያጠቃው የኖረው በዝናብ እጥረት ፤ በአንበጣ ፤ በረድና ትል መቅሠፍት ብቻ ሳይሆን ድንቁርና ስንፍና ፤ ሥራ አለመውደድንም ጭምር መሆኑ የታወቀ ነው ፤

፪ኛ/ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ሕዝቡን ከድንቁርናና ከድኅነት ለማላቀቅ የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ መርሐ ግብር (ፕሮግራም) አዘጋጅቷል ። ይኸንኑም ከልብ ተከታትሎ የሚያስፈጽም ጠቅላይ መምሪያ አቋቁሟል ። በትምህርት ማዕድ ላይ ያሉ ልጆቻችን ወንዶችም ሴቶችም ከመምህሮቻቸው ጋር ድንቁርናንና ችግርን ከአገራችን ሊያስወግዱ በአጭር ታጥቀው በቆራጥነት ተነሥተዋል ።

በዚህ የሥራና የዕውቀት የትምህርት ዘመቻ ቤተ ክርስቲያናችን በምትችለው መጠን መካፈል እንዲገባ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁሉ ሊያውቁት ይገባል ። ቤተ ክርስቲያናችን በአለፉት ኢያሌ ዘመናት በተቻላት መጠን ፤ ከሙሉ በክፍሉ ሠርታለች ። ያለፈውን በመተረክ ብቻ መቀመጥ መልካም ውጤትን ስለማይሰጥ በአሁኑ ጊዜ ፤ ያለፈውን... 

ያለፈውን በመተረክ ብቻ መቀመጥ መልካም ውጤትን ስለማይሰጥ በአሁኑ ጊዜ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተምሮ እንዲያውቅ ጊዜ ያዊ ወታደራዊ መንግሥት በአዘጋጀው የትምህርት መምሪያ መሠረት በየሀገረ ስብከቱ የምትገኙ ሰባክያን የገዳማት የአድባራትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ካህናትና መምህራን መዘምራንም ድንቁርናን ለመደምሰስ ዘማቾች ልጆቻችን ሲመጡ በደስታ ተቀብላችሁ በየአጥቢያችሁ ከሕዝቡ ጋር እንድታስተዋውቋቸው መልካም ሥራቸውም ይቃናላቸው ዘንድ ሁሉንም እንድታስተባብሩላቸው አደራ እንላችኋለን ።

የገጠሩ ሕዝብ ለእኔ በማለት ፈንታ ለእኛ በሚለው መሠረታዊ ፍልስፍና እንዲመራ የግል ጥቅምን ትቶ የጋራ የሆነ ችው አገራችን ኢትዮጵያ በትምህርት በሥራና በኤኮኖሚ ወደፊት እንድትራመድ ለማድረግ ከልብ እንዲሠራ መንግሥት ካሰለፋቸው ዘማኞች ጋር በመተባበር ማስረዳትና ማስተማር ዓይነተኛ ሥራችሁ ይሁን ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላው ከተማረ ፤ ድንቁርና ከተደመሰሰ ደዌ መራቆት ረኃብ ከሀገራችን ይደመሰሳሉ ፤ በኀዘን ፈንታ ደስታ ይተካል ፤ ስለዚህ በዚህ የተቀደሰ ዓላማ ከመተባበር ቸል እንዳትሉ አደራ እንላችኋለን ።

፫ኛ/ በድርቅ ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ክፍለ አገሮች ርዳታ ስለማድረግ ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞ ጀምሮ የችግረኞች መጠጊያ የድኩማን የእጓለ ማውታ ማደጊያ ሆና ኑራለች ። ይህም በዘመናዊ አመራር ሳይሆን እንኳ በአላት የቀድሞ ይዞታ የተቸገሩ ልጆቿን በደጅ ሰላምና በሰንበቴ ማኅበራት በሌላዎውም ብሔራዊ ድርጅት ስትረዳ መቆየቷ ያስመሰግናታል ። አሁን ግን አዲሱ የለውጥ ርምጃ በሚፈቅደው መሠረት መሥራትና ማሻሻል አስፈላጊ ስለሆነ ወታደራዊ መንግሥት ያቋቋመውን አስተባባሪ ኮሚሽን ለመደገፍና አስተለማስተባበር ቤተ ክርስቲያናችንም በልማት ኮሚሽን ሥር የድርቅ ቀበሌዎች አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁማለች ። ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን በአለፈው ይዞታዋ ብዙ ርዳታ አደረገች ለማለት ባንችልም በኢትዮጵያ ስለደረሰው የድርቅ ችግር በመጀመሪያ ለዓለም አብያተ ክርስቲያን ያስታወቀችና የገለጸች ቤተ ክርስቲያናችን ናት ከውጭ አገርም ርዳታ አግኝታ ፩፻፭ ሽህ ብር (አንድ መቶ አምስት ሽህ ብር) ለኮሚሽኑ አበርክታለች ።

ቀጥሎም ከውጭ እናቶቻቸውና አባቶቻቸው በረኃብ ምክንያት ያለቁባቸውና ሕጻናት ከወሎ አስመጥታ በአዲስ አበባ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት በማሳደግና በማስተማር ላይ ናት ። በደቡባዊ ክፍለ አገርም መጠነኛ ርዳታ አድርጋለች ።

ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት የቤተ ክህነትም ሠራተኞች ሁሉ በተቻላቸው መጠን በየክፍለ ሀገራቸው ረድተዋል ፤ ይህም ቤተ ክርስቲያናችን የምትችለውን ያህል ለመርዳት መሞከሯን መግለጻችን እንጂ በቂነው ማለታችን አይደለም ።

ለተራበ ማብላት ለተጠማ ማጠጣት ለታረዘ ማልበስ በጌቱ ቃላተ ወንጌል የታዘዘ ስለሆነ ችግረኞች እንዲረዱ ማድረግ ተቀዳሚ ሥራችን ነው ና ካህናተ እግዚአብሔር አዕይንተ እግዚአብሔር በየአጥቢያችሁ ቤተ ክርስቲያን ለድርቅ ቀበሌዎች መርጃ የተለየ የሙዳየ ምጽዋት ሣጥን በማዘጋጀት ርዳታ በተቻለ ፍጥነት እንድትሰበስቡ ፤ እህልና ልብስም ቢሆን የሚከማችበት አዘጋጅታችሁ እንድትቀበሉና ለዚህ በጎ ተግባር በተቋቋመው ኮሚቴ አማካይነት ርዳታው እንዲሰጥ ይደረግ ዘንድ እናሳስባለን ። ይህን ለመፈጸም ፍጹም የሆነ ፈቃደኝነትን ይጠይቃልና ደስ እያላችሁ ለምእመናን በመግለጽ ማስተባበር ያሻል ምእመናንም የካህናትን ቃለ ምዕዳን በመስማት እግዚአብሔር ከሰጣቸውና ከባረከላቸው ሀብት ከመስጠት ቸል እንዳትሉ በእግዚአብሔር ቃል እንነግራችኋለን ።

፬ኛ/ በትዕግሥትና በበጎ ምግባር የታወቀው ጻድቁ ኢዮብ ራቁቱን የሆነው ሰው ሲጠፋ ወይም ድኃ ያለ ልብስ ሲሆን አይቼ እንደሆን ፤ ጎንና ጎኑ ያልባረከችኝ በበጎቼም ጠጉር ያልሞቀ እንደሆነ ትከሻዬ ከመሠረቱዋ ትውደቅ ክንዴም ከመገናኛዋ ትሰበር» ብሏል ። መጽሐፈ ኢዮብ ፴፩ ቍ፡ ፲፱—፳፪ ።





www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ምእመናን ሁሉ እንደተለመደው በአገራችን አሁን ከመጠን በላይ ድርቅ በበዛበት ችግር በጸናበት ጊዜ እጃቸው ለስጦታ እንዲዘረጋ ማድረግ መንፈሳዊ ግዴታቸው ነው ። ለድሆችና ለድሀ አደጎች ፍረዱ ፡ ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅ አድርጎ ፣ ብቸኛው ንና ችግረኛውን አድኑ ይላል ። መዝሙረ ዳዊት ፹፩ ቍጥር ፫—፬። ስለዚህ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቸገሩትን ወገኖቹን ለመርዳት በአንድነት መተ ባበር ትንሣኤ ልቡና ይነሣ ዘንድ አደራ እንላለን ።

ቸር አምላካችን የኢትዮጵያን መልካም ርምጃ ይባርክ ።



## ቅዱስ ፓትርያርኩ ለ፲፱፻፹፯ ዓ፡ ም፡ ዓቢይ ጾም መግቢያ ያደረጉት ቃለ ምዕዳን

ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የ፲፱፻፹፯ ዓ ም የዓቢይ ጾም መግቢያን ምክንያት በማድረግ በሬዲዮና በቴሌቢዥን ለመላው ምእመናን የካቲት ፴ ቀን የሰጡት ቃለ ምዕዳን ።

ወይእዜኒ ተመየጡ ኀቤየ በኵሉ ልብክሙ በጾም ወበጸሎት ወአነሂ እትመየጥ ኀቤ ክሙ ይቤ እግዚአብሔር ።

የተወደዳችሁ እግዚአብሔር የመረጣችሁ በክቡር ደሙ የዋጃችሁ ምእመናን ሆይ ፤ የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን ።

እንደምታውቁት በነባሪቱ በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት ታላቁ ጾማችን መግባቱ ነው ፤ ክርስቲያኖች አባቶቻችን ይህን ዐቢይ ጾምን የተቀበሉት ከመ ድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ፤ የጾም ሥርዓት በተ ስፋ ትንቢት የነበሩ አበውን በፍጻሜ ትንቢት በሀብተ ወልድና የከበሩ ውሉድን ታስተ ባብራለች ፤ ኃጢአትን ታስተሠርያለች ፤ ከባዱን ነገር ሁሉ ታቃልላለች ፤ የጠመመውን ታቃናለች ፤ የጎደለውን ትሞላለች ፤ መለያየትን ታርቃለች ፤ ኅብረትን ሰላምን ታመጣለች

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ያሰበውን ቸርነት በጾም ጀምሮ በጾም መጨረሱን በሥራ በቃል ከሰጠው መግለጫ እንረዳለን ፤ ይህም ሰው በጾም ኃይል ሰውነቱን ይልቁንም ብርቱ ጉልበት ያለውን ሕሊናውን ለመግዛት እንደ ሚችልና በሃይማኖት በጾም በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የእግ ዚአብሔርን ረድኤት አጋዥ አድርጎ በሥጋው በነፍሱም ከኃሣር ወደክብር ፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከድንቁርና ወደ እውቀት ፤ ከሞት ወደ ሕይወት ሊሸጋገር መቻሉን ያሳየናል፤ ልዑል እግዚአብሔር አሁንም በፍጹም ልባችሁ በጾምና በጸሎት ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ብሏል ።

ምእመናን ሆይ ፤ የአሳብ ሞገድ በሰፈነበት የኃዘን ማዕበል በሚዋኝበት በዚህ ባሕረ ዓለም የሚኖር ሁሉ በዚህ ተስፋ ሕይወት ተመርቶ የሃይማኖት መልሕቁን በምሕረቱ ወደ ቸር አምላክ ላይ መጣልና የልቡናውን መርከብ ማጽናት ፤ ማቆም ፤ ፀጥ ማድረግ ይገባዋል ፤ በዚህም ወደ ሰላም ጎዳና ሊመራ ይችላል ፤ አባትህን ጠይቀው ይነግረሃል ነውና እስኪ ነቢዩን አንዳንድ ነገር እንጠይቀው ተራቡ ፤ ተጠሙ ነፍሳቸውም ተጨነቀ ባቸው ፤ በጨነቃቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ እርሱም ፤ ከመከራቸው አጸናቸው፤ ቀናውን መንገድ መራቸው፤ በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ከመከራቸው አዳ ናቸው ዕረፍት አግኝተዋልና ወደወደዱት ወደብ መርቶአቸዋልና ደስ አላቸው ይላል የሰው ኑሮ ወጣ ገባ መሆኑ የታወቀ ነው ችግር የተጫነው ረኃብተኛ የታመመ በሽተኛ መንገድ የጠፋበት መንገደኛ ፤ ማዕበል የሚያንገላታው መርከበኛ ብልሃቱ የጠፋበት ችግረኛ ከፈለጉት በቶሎ ሊያገኙት በሃይማኖት ሊደገፉበት የሚቻላቸው ሁሉ ፤ የሚቻ ለው ምንም ነገር የማይሳነው አንድ ኃይል አለ ።

እሱም እግዚአብሔር አምላክ ነው ፤ ወደዚህ ኃይል አምላክ ለመድረስ በሃይማ ኖት በጾምና በጸሎት መቅረብ ያሻል ፤ አሁንም በሃይማኖት በጾምና በጸሎት በምጽዋት በኃዘንና በልቅሶ ወደ እሱ እንቅረብ ፤ ወደ እርሱ ቅረቡ እርሱ ያበራላችኋል ተብሏልና ፤



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በሥራችን በጾማችን በጸሎታችን ውስጥ ጨው ይኑር ፤ እሱም ፍቅር ነው ፤
በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም አቅጣጫ ብንመለከት ሃይማኖት ፤ ምጽዋት እውቀት ፤
መሥዋዕትነት የተባሉትንና ሌሎችም የሚመስሏቸውን የሰው የኑሮ ቅመሞችን ሁሉ
የሚያዛምተው የሚያስማማቸው የሚያጣፍጣቸው ፍቅር ነው ።

የሰው ኅብረቱ ማሠሪያዎች ፤ ሃይማኖትና ተስፋ ናቸው ፤ ከሁሉም ፍቅር ይበልጣል
ተብሏል ፤ እንደምታውቁት በሀገራችን ከደረሰው ከድርቁ ከረሃቡ ሌላ በሰሜኑ ክፍል
የደረሰው አሳዛኝ ነገር አገራችንን የሚጎዳ መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ጠላት በወንድማማቾች
መካከል ገብቶ የራሱን ፍላጎት ለመፈጸም ወንድማማቾችን ሲያስተላልቅ ከማየት የበ
ለጠ አስከፊ ነገር የለም ፤ እንዲህ ከሆነ በባላጋራህ እወቅበት ባለው በጌታችን ቃል ተረ
ድተን በፍቅር ጸንተን መለያየትን አርቀን አንድነትን አጥብቀን ብንሠራ የጠላት ኃይል
ይሰበራል አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነን በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ብንጮህ
ከባዱ ነገር ሁሉ ይቃለላል ። በሀገራችን በሕዝባችን መካከል መለያየት ፀብ ክርክር
ርቆ ሰላም አንድነት ይመሠረታል ።

የኢትዮጵያን ታሪክ ስንመረምር ለአንድነቱ ጽንዓትና ለሀገሩ ነጻነት ሁሉም በያ
ለበት የሚፈለግበትን ተልእኮ እንደፈጸመ በግልጽ እንመለከታለን ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ፤ ባህል ፤ አቀዋምና ጠባይ ከሌሎች አህጉር የሚለይበት
ዐቢይ ምክንያት ለረጅም ዘመናት በጠላቶቿ ብትከበብም የራሷን የኑሮ መሠረትና
መልክ እንደጠበቀች ለረጅም ዘመናት በነጻነት ተከብራ መኖሯ ነው ።

ይህን ዛሬ የምንኰራበትን ነፃነት ለመጠበቅ ባለፉት ዘመናት በተደረገው ብርቱ
ተጋድሎ ከየክፍለ ሀገሩ ቤታቸውን ዘግተው ትዳራቸውን ፈትተው ከባድ ችግር ያሳለ
ፉት የጎስቆሉ በቆራጥነት ለሀገራቸው ነጻነትና አንድነት ሕይወታቸውን የሠው ኢትዮ
ጵያውያን ፤ እጅግ ብዙ ናቸው ፤ ለአብነት ያህል የመሪዎቹንና የስመ ጥሩ ጀግኖቹን ስም
እዚህ ላይ ለመጥቀስ ብንመኝም እንኳ ብዙ ስለሆኑ ጊዜ ይወስድብናል ።

አስተዋይነታችን ሊያርፍበት ፤ የሚገባው ታላቁ ቁም ነገር አብዛኛው ታሪካዊ ተጋ
ድሎ የተፈጸመው በዚሁ በቀይ ባሕር ምክንያት አሁን ኤርትራ ተብሎ በሚጠራው
ጥንት ግን ባሕረ ነጋሽ ተብሎ ሲጠራ በኖረው ክፍለ ሀገር ላይ መሆኑን ነው ።

የፍየል ዓይን ወደ ቅጠል ፤ የነብር ዓይን ወደ ፍየል እንዲሉ የኢትዮጵያዊው ሕዝብ
ዓይንና ልብ እግዚአብሔር ፈጥሮ የሥልጣኔ መዝለቂያና የሀብት ምንጭ በሆነው ባሕር
ላይ ሲሆን የጠላቶች ዓይን ደግሞ የመርዛቸው ማሠራጫ ሊሆን በሚመችበት ባሕርና
እርሱን አልፎ በሚገኘው ለም መሬት ላይ ነው ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በባሕር
ከልሎ በተራራ አገሮች ባርኮ ለኢትዮጵያውያን የሰጠውን አገር በየጊዜው ፈተና ቢበ
ዛበትም በረድኤቱ ሳይለያት በጀግኖች ልጆቿ አድሮ ሲከላከልላት እንደኖረ ታሪክ ራሱ
ይመሰክራል ፤ ጠላት ሠርጎ ባንዳንድ ክፍል ለመግባት የቻለበት ጊዜ ቢኖርም ብዙ ዕድ
ሜና ፋታ ሳያገኝ በመጣበት መንገድ እንደወረቀት ተጠቅልሎ ፤ እንደጉም በኖ ሲጠፋ
ያየንበት ጊዜ እንኳ በታሪክ መነጽር የሚታይ ሳይሆን በቅርብ የትናትና ስለሆነ አብዛ
ኛዎቻችን በሕይወት የምንገኝ ምስክሮች ያለንበት ነው ።

በተለይም ኤርትራ ክፍል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን የባዕድ ቀንበር
ተሸክመው በኖሩበት ጊዜ ኢትዮጵያዊ ታሪካቸውን ፤ ባህላቸውን አቀዋምና ጠባያቸውን
ሳይለውጡ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜታቸው ሳይቀዘቅዝ ኖረው በእግዚአብሔር ቸርነት
ጠላት ከገራችን እንደወጣ ለጊዜው ሌላ ቢተካባቸው እንደገና ትግላቸውን ቀጥለው



በውጭ ገንዘብና ፕሮፓጋንዳ ሳይበገሩ ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማግኘት መብታታ
ቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተደናቂነት የተለየ ዓምድ መያዝ የሚገባው ነው ።

የኢትዮጵያን ታሪክ በሌላ በኩል ስንመለከተው በሀገራችን ውስጥ በአስተዳዳሪዎች
በቀበሌዎችና በሠፈርተኞች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር መጀመሪያ ጉዳያቸውን
በሽማግሌ ተላልከው ለመፈጸም ይሞክራሉ ፤ በተመረጡ የአገር ሽማግሌዎች መፈጸም
ሳይቻል ሲቀር ለሀገራቱ መሪ በማመልከት ችግሩ በሰላም ሲፈጸም ኖሯል ። ይህም የኢ
ትዮጵያ ሕዝብ ያለውን መተሳሰብና ትዕግሥት የሚገልጽ ነው ።

ስለዚህ የደረሰውን ችግር ሁሉ ቀርቦ በመነጋገር እንደየደረጃው በሰላም ሊፈጸም
ሲገባው ፤ ሰላምን ሳንጠቀምበት የሰላም ተቃዋሚዎች ሆነን ብንገኝ የራስን ብቻ ሳይሆን
የቤተ ዘመድን መሠረታዊ ነፃነት ከማሳጣታችንም በላይ የሀገርን ዕድገትና ልማት ማሰ
ናከል ነው ። ተበደልሁ በሚለው ክፍል ላይ ተጨማሪ በደል ያስከትላል ። ንብረቱን ያባ
ክናል ፤ የበለጠ ችግር በኑሮው ላይ ይደርሳል ።

በአስተዳደር በኩል በደል አለ ካልን የተበደለውና የሚበደለው ኢትዮጵያዊ የሆነ
ሁሉ ነው ። አለበለዚያማ በዳዩስ ተበዳዩስ ማን ሊሆን ይችላል ? ወቃሹስ ማን ነው ?
የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላው አይደለምን ? ይህን ዓይነት በደል ከሚመለከተው የአስ
ተዳደር ክፍል ጋር በመወያየት መፍትሔ ማስገኘት ያለበት በደሉን በቅድሚያ ተረድቻ
ለሁ የሚለው ክፍል ነው ። ዓይን የሚያየውን ፤ ጆሮ የሚሰማውን ፤ እጅ የሚዳስሰውን
ነገር እንደሌለ ቈጥሮ በግል ፍላጎትና ስሜት ብቻ እየተመሩ ለኢትዮጵያ ሀገራችን ልማት
የሚጠቅሙትንና እንደማናችንም የመኖር ነፃነት ያላቸውን ፤ ሽማግሌዎች ፤ ባልቴቶች፤
የተማሩ ወጣቶችና ሕፃናት ደም በከንቱ እንዲፈስ ምክንያት ከመሆን የከበደ ጥፋት
ይኖር ይሆን ? በየትም የዓለም ክፍል ቢሆን ጦርነት የሚዋጉለትን ክቡር የሰው ነፃነት
ከመደምሰሱ ሌላ የተረፉትን ሰዎች ሠርቶ ለመኖር የሚረዳቸውን ሙሉ አካልና የል
ማት ዕቅድ ማበላሸት ይቅርታ የማያሰጥ ሥቃይ ሲፈጥር ኖሯል ።

ከዚህም አልፎ የማያስፈልግ በሽታና ረሃብን ያስፋፋል ። ይህ እንደዚህ መሆኑ ከታ
ወቀ ጦርነት ማድረግ ማንን ለመጥቀም ነው ?

ኢትዮጵያ አንድ አካል ናት ። የአንዱ አካል ክፍል ቢታመም ሁሉንም አካላት ይሰ
ማዋል ። በአንድ ክፍል የተጀመረው ሁከት በጠቅላላ የኢትዮጵያን ሰላማዊና ፈጣን ዕድ
ገት ወደ ኋላ በመጎተት እንደሚበድለው ሁላችንም መረዳት አለብን ።

የሰው ልጅ ከዓለምና በተለይም ከራሱ ታሪክ ካልተማረ ወደፊት የመራመዱ ጉዳይ
ተረት ይሆንበታል ። ያለፈው ታሪካችን ይበጅም ይከፋም ወደፊት የምንመራበትን
እቅድ የምንመሠርትበት ጽኑዕ አለት መሆኑን መዘንጋት አይቻለንም ።

ስለዚህ ካህናት በጸሎት ፤ በትምህርትና በስብከት ፤ ወጣቶች ትምህርታቸውን አቋ
ርጠው የገጠሩን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ፤ ሌላውም በየተመደበበት ተግባር ለዕድገት
በሚጣደፍበት በአሁኑ ጊዜ ለዚህ ተገቢ ተግባር በሙሉ ልብ መሳተፍ ሲገባ ለሀገራችን
ሰላም ፤ ለዕድገታችን እንቅፋት ፤ ለአንድነታችን ጥፋት መፍጠር ማስተዋልን አያመለ
ክትም ።

በአንድ ኅብረተ ሰብዕ ውስጥ ያለ ቅያሜ በራስ ቤት ውስጥ ወደ ፍቅር መለወጥ
ሲቻል በምንም ለማይጠቅም ዓላማ ወደ ጎረቤት ማዛመቱ በአዛውንቱና በወጣቶች ላይ
ከፍተኛ የሕሊና ኃላፊነት ስለሚያስከትልባቸው በእግዚአብሔርም በሰውም ፊት ያስ
ጠይቃቸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማማለድና ማስታረቅ ፣ ሰላምም በየቤቱ እንዲፈጠር ማድረግ የተለመደ ባሕርዩ ሲሆን ፣ አሁን በኤርትራ ክፍለ ሀገር የተፈጠረውን ሁኔታ አበው እን ዴት ዝም ብለው ሊመለከቱት ይችላሉ ?

ኢትዮጵያውያን የዓለምን ጠቅላላ ሁናቴ አጠቃለው በተገነዘቡበት በአሁኑ ጊዜ ቀርቶ በውጭ ጠላቶች ተከበው ከዓለም ሕዝብ በመላ ተለይተው በኖሩበት በድሮው ጊዜ እንኳ ወንድ ፣ ሴት ካህን ፣ ምእመን ሳይሉ ሲጋደሉለት የኖሩትን ቤሔራዊ ጉዳይ ሁሉ ምንም ጉዳት ሲደርስ ሲያዩ በቸልታ ያልፉታል ተብሎ የማይታሰብ ነው ።

ስለዚህ ኤርትራውያን አበውና በጠቅላላውም ወላጆች ሁናቴው የባሰ ጥፋት ሳያ ስከትል ፤

፩ኛ/ ጉዳዩን ሳይረዱ ወደጥፋት ጐዳና የሚመሩትን ልጆቻቸውንና ወንድሞቻ ቸውን በመምከር ፣

፪ኛ/ በተለይ በኤርትራ ላይ የተፈጸመ በደል አለ ከተባለ ፣ አለ የሚባለውን በደል በዝርዝር አለስተዳደሩ በማቅረብ ችግራቸውን ሁሉ በውይይትና በመግባባት እንዲ ወገድ እንዲያደርጉ ፣

፫ኛ/ በጥፋት ጨለማ ተውጠው ስለሚገኙ ኤርትራውያን ወንድሞቻችንና እኅ ቶቻችን እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያ የተቀደሰ አንድነት ፣ ርምጃና ሰላም ብለው በማንኛ ውም ዝርዝር ጉዳይ ላይ ውይይት አድርገው ሰላም እንዲያወርድ በቤተ ክርስቲያን ስም አጥብቄ እየጠየቅሁ ፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ አሳዛኝ ጉዳይ ሰላማዊ ፍጻሜ እንዲያገኝ ምህላና ጸሎት እንዲያደርግ የአባትነት ልመናየን አቀርባለሁ ።

ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ ፣ በፍጹም ልባችን በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እን መለስ ፣ እግዚአብሔርም በምሕረት ወደ እኛ ተመልሶ ሀገራችንን ባንድነት በኅብረት እንዲያጸናልን ቸርነቱን እንዲያበዛልን እንለምነው ።

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ይባርክ ፣ ለኢትዮጵያና ለመ ላው ዓለም ሰላሙን ይስጥ

ምስጋና ለርሱ ይሁን ።
አ ሜ ን ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ስለበዓላትና አፅዋማት

## ሕዝቡ አስተያየቱን እንዲሰጥበት ያስተላለፈው ውሳኔ

ሕዝቡ አስተያየቱን እንዲሰጥ ያስተላለፈው ውሳኔ

በብፁዕ ወቅ/አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ መን በርነት የተካሔደው ቅዱስ ሲኖዶስ በዓላትና አጽዋማትን በሚመለከተው ጉዳይ ሰሞ ኑን ተሰብስቦ በዓላትና አጽዋማትን በሚመለከቱት ጉዳዮች ላይ ከስድስት ዓመታት በፊት የመከረበት ቢሆንም ከውሳኔው በፊት ምእመናኑ እንዲተቹበትና አስተያየት እንዲሰጡ በት በሲኖዶስ ያስተላለፈው ውሳኔ ።

ከዚህ ቀደም በግንቦት ፯ ቀን ፷፩ ዓ/ም በተደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ፤ ለአጽዋማትና በዓላት አከባበር መምሪያ የሚሆነውን ጽሑፍ ፤ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ብፁዕ አቡነ ቄር ሎስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ፤ ክቡር ንቡረ ዕድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት በዚሁ ልዩ ኮሚቴ ተጠንቶ የቀረበውን አስ ተያየት ፤ አንድባንድ በንባብ ካዳመጠ በኋላ ነው ።

«ቅዱስ ሲኖዶሱ በዚሁ ጉዳይ ላይ ንግግር ካደረገበትና አሳብ ለአሳብም ከተለዋወ ጠበት በኋላ ፤ ጉዳዩ ካህናቱን ብቻ ሳይሆን ፤ ሕዝበ ክርስቲያኑንም በቀጥታ የሚመለ ከት በመሆኑ ፤ ይኸው በልዩ ኮሚቴው ተጠንቶ የቀረበው አሳብ ፤ በጋዜጦች ፤ በሬዲ ዮና ቴሌቪዢን ከተገለጠ በኋላ ፤ ሕዝቡ ይተችበት በማለት ወስኗል ። የመጨረሻው ውሳኔ የሚደረገውም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፤ መምህራንና ካህናት ፤ ምእመናኑም አውቀውት አስተያየታቸውንና አሳባቸውን ፤ ከገለጡበት በኋላ መሆኑን አረጋግጧል ።

ሲኖዶሱ ለውሳኔው መነሻ ያደረገውም «ሐዋርያት በ፴ኛው ትእዛዝ ቍጥራቸው ፸፩ ከሚሆኑት ቀናት ፤ በ፴ኛው ትእዛዝ ከሚገባው ሥራ ያጎደልነው ቢኖር ፤ ለሁላችንም የእግዚአብሔር መንፈስ አለንና እናንተም በሚገባ ፍረዱ ። ከዚያም በ፴፰ኛው ከእኛ ምንም ያስቀረነው ቢኖር ኤጲስ ቆጶሱ ያሳስብ ። ዳግመኛም ከዚሁ ከ፴፯ኛው ቀኖና የተወደዳችሁ ምእመናን ሆይ ! ከኛ ምንም የቀረ ቢኖር እርሱንም ለሚገባው ሰው እግዚ አብሔር ይግለጥለት ። ቤተ ክርስቲያን ወደ ፅጥታና ወደወደብ ትደርስ ዘንድ ፤ በዲድስ ቅልያም በ፩ኛው አንቀጽ ሐዋርያት ጌታችን ፤ እናንተንም በምድር ያሠራችሁት በሰ ማይ የታሠረ ይሁን በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሁን ብሏችኋልና እንደ አምላክ በሥልጣናችሁ ፍረዱ የሚለውን ቃል ነው ።

ልዩ ኮሚቴው ባቀረበው አሳብ ላይ በሳምንት የሚከበሩትን ቅዳሜና እሑድን ፤ በዓመት የሚከበሩትን ተሰዓቱ በዓላትን ፤ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን ዓበይት በዓላትን ፤ የመላእክትን በዓላት አከባበርን ፤ የሐዋርያት በዓላት አከባበርን ፤ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበሩትን በዓላት ዝርዝር አቅርቧል ።

እንዲሁም ስለጾም ጠቃሚነት ሲያስረዳ ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፵ ቀን የጾ መውን ጾም ምሳሌ አድርጎ ጠቅሷል ። ኮሚቴው በዚሁ ጥናት ላይ ጾመ ነቢያት ወይም የታኅሣሥ ጾም ፤ ጾመ ሐዋርያት ወይም የሰኔ ጾም እንደ ዓበይት አጽዋማት የማይቈጠሩ መሆናቸውን አስረድቷል ።

ከኮሚቴውም የቀረበው አስተያየት ፍሬ ነገር የሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ በዘመነ ብሉይ የነበሩት በዓላት አከባበር ።

እግዚአብሔር በጥንተ ፍጥረት ፯ ቀን ፍጥረታትን ፈጥሮ በ፯ኛው ቀን ሥራውን ፈጽሞ ዐርፏል ። ስለዚህ ጌታ ለሙሴ ከሰጠው ከ፲ሩ ትእዛዛት አንዱ አክብር ሰንበቶ ፣ ሰንበትን አክብር ያለው ነው ። በዚህም መሠረት ሰውና ቤተሰቡ ፤ እንስሳውም ይረፍ በት ተብሎ ሥርዓት ተሠርቷል ። ከዚህም በኋላ በወር በወሩ ሠርቶ ወርኅ እንዲከበር ታዞ ነበር ። እንዲሁም በዓመት ፫ ጊዜ የሚከበሩ ዓበይት በዓላት ፤

ሀ/ በዓለ መጸለት ፤
ለ/ በዓለ ናዕት ፤
ሐ/ በዓለ ሰዊት እንዲከበሩ ታዞ ነበር ።

በዚህ መሠረት በዘመነ ሥጋዌ ፤ ከዘመነ ሥጋዌ በኋላ ከሐዋርያት ጀምሮ ሠለሥቱ ምዕት ፤ ከሠለስቱ ምዕት በኋላም የተነሡ ሊቃውንት በዓላት እንዲከበሩ እንደሚከተለው አዘዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ሀ/ በሳምንት ከሚከበሩት ቀዳሚትና እሑድ ፤ ለ/ በዓመት ከሚከበሩት ተሰዓቱ በዓላት ፤ እነዚሁም ፩ኛ/ መጋቢት ፳፱ ቀን ጌታችን የተጸነሰበት ፤

፪ኛ/ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ጌታችን የተወለደበት ፤

፫ኛ/ ጥር ፲፩ ቀን ጌታችን የተጠመቀበት ፤

፬ኛ/ በዓለ ሆሣዕና ፤

፭ኛ/ በዓለ ስቅለት ፤

፮ኛ/ በዓለ ትንሣኤ ፤

፯ኛ/ በዓለ ዕርገት

፰ኛ/ በዓለ ጰራቅሊጦስ ፤

፱ኛ/ በዓለ ደብረ ታቦር ናቸው ፤

፪ኛ/ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ዓበይት በዓላት ።

ሀ/ ግንቦት ፩ ቀን ልደቷ ፤

ለ/ ኅዳር ፳፩ ቀን ጽዮን ፤

ሐ/ ጥር ፳፩ ቀን አስተርእዮ (ዕረፍቷ)

መ/ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፍልሰቷ ናቸው ።

ከነዚህም ሌላ ፤ የታኅሣሥ በዓታ ንና የየካቲት ኪዳነ ምሕረትን የመሳሰሉ የእመቤታችን በዓላት መታሰቢያዎች በበዓላቶቹ ስም ቤተ ክርስቲያን በታነፀበት ይከበራሉ ።

፫ኛ/ የመላእክት በዓላት አከባበር ።

ሀ/ ኅዳር ፲፪ ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል ፤ ለ/ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን የቅዱስ ገብርኤል በዓል ፤ ሐ/ ሰኔ ፲፪ ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል ፤ እንደዚሁም የቀሩት መላእክት ፤ በዓላት በየስማቸው ቤተ ክርስቲያን በታነፀበት ቦታ በዓመት አንድ ጊዜ ይከበራል ።

፬ኛ/ የሐዋርያት በዓላት አከባበር ።

ሀ/ በየዕረፍታቸው ቀን በዓመት አንድ ጊዜ ይከበራሉ ፤ ለ/ የጻድቃንና የሰማዕታት በዓላት ፤ በየስማቸው ቤተ ክርስቲያን በታነፀበት ቦታ በዓመት አንድ ጊዜ በየዕረፍታቸው ቀን ይከበራሉ ።

ከእነዚህም ሌላ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበሩ ፤ ሀ/ መስከረም ፩ ቀን የዘመን መለወጫ ፤ ለ/መስከረም ፲፯ ቀን መስቀል ፤ ሐ/ ጥር ፲፪ ቀን ቃና ዘገሊላ ፤ መ/ማዕዶት ፤

እነዚህም በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበሩ የታወቁ በዓላት ናቸው ። ሕዝቡ ግን እንደልማድ አድርጎ ዛሬ በየወሩ የሚያከብራቸው በዓላት በዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የተሠሩ ናቸው እንጂ ፤ ሲኖዶስ አውቋቸው የምእመናን ፤ ግዴታ ሆነው የሚከበሩ አይደሉም ይህን ለመግለጥ ያደረሰን ፤ ሐዋርያት ሠለስቱ ምዕት ፤ ከነሱም በኋላ የተነሡ ሊቃውንት በዓመት እንዲከበሩ ውሳኔ ያደረጉላቸው በዓላት እነዚህ ከይላ የተነገሩት ሲሆኑ ፤ ሕዝቡ በልማድ የየወሩን በዓላት ከማክበሩ የተነሣ ፤ ዓበይት በዓላት ተረስተውና ተሽረው ስለተደፈሩ ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ዓበይት በዓላት ብቻ እንዲያከብር ያልተጠቀሱትን ሕዝቡ እንዲሠራባቸው ፤ ቢሆንም በዓለ እግዚአብሔር በዓለ ማርያም ፤ በዓለ ሚካኤል በየወሩ በማኅሌትና በቅዳሴ ብቻ ሊፈጸም ይችላል ።

፭ኛ/ ስለ አጽዋማት ።

ጾምሰ ጸባሕተ ሥጋ ውእቱ በከመ ምጽዋት ጸባሕቱ ንዋይ ይእቲ እንደተባለው ፤ ምጽዋት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ገንዘብ ግብር እንደመሆኑ ፤ ጾምም ምእመናን ሥጋቸውን ለነፍሳቸው ለማስገዛት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የሰውነት አገልግሎት መሥዋዕት ነውና ምሥጢሩን አውቀው ቢጾሙት ይጠቅማል ።



ስለዚህ ለሐዲስ ኪዳን መሠረቱ ብሉይ ኪዳን እንደሆነ ፤ ለሐዲስ ም ኪዳን አጽዋማት መሠረታቸው አጽዋማተ ብሉይ ናቸው ። የብሉዩን አጽዋማት ሊቀ ነቢያት ሙሴ ክርሱም ቀጥሎ በየጊዜው የተነሡ ነቢያት ጾመዋል ። በዘመነ ሐዲስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢያትና አሪትን ልሽር አልመጣሁም በሚል ዓዋጅ አጽንቶ ፵ ቀን ጾሟል ። ሐዋርያትና ሠለስቱ ምዕትም የጌታን ጾም መሠረት በማድረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ፵ ጾም ፤

ሀ/ ረቡዕ ፤ ዓርብ ፤ ለ/የልደት ገሐድ ፤

ሐ/ የጥምቀት ገሃድ ፤ መ/ ጾመ ነነዌ ፤

ሠ/ ጾመ ፍልሰታ ፤ እነዚህ የተለመዱ አጽዋማት ናቸው ።

እነዚህም አጽዋማት በሆስፒታል በጽኑ ደዌ ለሚገኙ ሕሙማን ሐኪም መድኃኒት አዞላቸው ለሚታከሙ ፤ በመምህረ ንስሓቸው አማካይነት ሐኪም ያዘዘላቸውን እየተመገቡ ሊታከሙ ይችላሉ ። ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ፤ ቤተ ክርስቲያን ስለአጽዋማት ማሻሻያ ልታወጣ ያሰበችበት ምክንያት ፤ ዘመን ያመጣውን ችግር ለማቃለል ቢሆንም ፤ እነዚህኑ አጽዋማት ለመጾም ቦታና ጊዜ ለማይፈቅድላቸው ።

፩ኛ/ ወሰን ለመጠበቅ በየበረሃው ለሚገኙ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት ፤

፪ኛ/ በአየርና በባሕር ፤ በየብስ ለሚጓዙ መንገደኞች ፤

፫ኛ/ በየፋብሪካው በሥራ ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች ፤ ፬/ ከፍተኛ ጥናት ባለው በትምህርት ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ከጥሉላት ምግብ በቀር ጧት ቁርስ ቢበሉ ሻይና ቡና ቢ ጠጡ ይፈቀዳል ።

በዚህም መሠረት በየሀገረ ስብከቱ የሚገኙት ሊቃነ ጳጳሳት ከባድ ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች ችግሩን እያዩ ፤ በአስተያየት ማሻሻያ ሊሰጡ ይችላሉ ። ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት አጽዋማት ሌላ ፤

ሀ/ ጾመ ነቢያት (የታኅሣሥ ጾም)

ለ/ ጾመ ሐዋርያት (የሰኔ ጾም) ናቸው ።

እነዚህ ሁለቱ አጽዋማት እንደዓበይት አጽዋማት ስለማይቈጠሩ የጾሙ መታሰቢያነት እንዳይረሳ ያህል ፤ የነቢያትና የሐዋርያት ጾም ለሕዝቡ ሲባል፤ ካልጾሙ ፋሲካ ፤ ካላዘኑ ደስታ አይገኝምና በየአጽዋማቱ መጨረሻ አምስት አምስት ቀን በመጾም የክርስቶስ ልደትና የሐዋርያት ዓመት በዓል ርእንዲከበር በማለት ከኮሚቴው አስተያየት ቀርቧል ።

## ስለተዘዋዋሪ ሰባኪዎች ከሲኖዶስ የተሰጠ ውሳኔ

የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ መስከረም ፳፬ / ፹፯ ዓ/ም ባሳለፈው ውሳኔ ላይ በቅዱስ ሲኖዶስ ታውቆ ሳይጠና የስብከት ፈቃድ አለን እያሉ የሚያወናብዱትን ተንኮለኞች የየአድባራቱ ኃላፊዎች ቊጥጥር እንዲያደርጉ በማስጠንቀቅ ቀጥሎ ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል ።

ብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ፤ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና እንዲሁም የገዳማት መምህራንና ቆሞሳት በተገኙበት በየአብያተ ክርስቲያናቱ በዓላት ቈጥረው ስለ

www.ethiopianorthodox.org

ማ.ዘዋወሩ ሰባክያን ነን ባዮች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ውሳኔ ተሰጥቷል ።
ማ.ዘዋወሩ ሰባክያን ነን ባዮች የሕዝቡን ገንዘብ በማታለል ለመዝረፍ በዓላት
፩ኛ/ አንዳንድ ሰባክያን ነን ባዮች የሕዝቡን ገንዘብ በማታለል ለመዝረፍ በዓላት
እየቈጠሩ በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመዘዋወር የሚያደርጉት ስብከት ከሃይማኖት ሥር
ዓት የወጣ የስድብና የዘለፋ ቃል ምእመናንን ከቤተ ክርስቲያን የሚያርቅ ፤ አንድነትን
የሚነጣጥልና ሰላምን የሚነሣ መሆኑ ተደርሶበት ፤ ከነዚህ አንዳንዶቹ በቤተክርስቲያን
ተወግዘው የተለዩ መሆኑ ታውቋል ።

፪ኛ/ ከነዚህም ከተወገዙት ሌላ ግብረ አበሮቻቸው የሆኑ ሰባክያን ነን የሚሉ ብዙ
አወናባጆች መኖራቸው ግልጽ ነው ፤ ይህም አድራጎት በቸልተኝነት ቢታለፍ ኃላፊነት
በሌላቸው ሰዎች አንደበት የሚነገረውስብከት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን እንዲሁም
በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መለያየት የሚያስከትል አስጊ ሁኔታ ስለሚፈጥር አሁ
ኑኑ በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል ። እነዚህም ቤተ ክርስቲያንን እየተጠጉ ሕገ ወጥ ተግ
ባር የሚፈጽሙት በፖሊስ ኃይል እንዲወገዱ ለማድረግ በየጊዜው ሳይሞከር አልቀረም ።

፫ኛ/ ቅዱስ ሲኖዶስ ሳያውቀውና ሳይጠና ማንነታቸው ወይም የሚከተሉት እም
ነት ሳይመረመር የተሰጠን የስብከት ፈቃድ አለን በማለት ማስቸገራቸው ስለታወቀ፤
በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን ጠባቂ እንደሌላት የማንም መፈንጫ ሆና እንድትገኝ
አድርገዋል ።

ስለዚህ ይህ አድራጎት እየቀጠለ እንዳይሄድ ጥንቃቄ ማድረግ ስለሚያሻ ፤
ስለዚህ ይህ አድራጎት እየቀጠለ እንዳይሄድ ጥንቃቄ ማድረግ ቀርበው ፈተና
ሀ/ ከዚህ ቀደም የስብከት ፈቃድ የተሰጣቸው ቢኖሩ እንደገና ቀርበው ፈተና
ተቀብለው ችሎታቸው ታውቆ የሚገባቸው ሆነው ሲገኙ አዲስ የተዘጋጀውን ፈቃድ
ካላገኙ በስተቀር በየአብያተ ክርስቲያናቱ ም ሆነ በማንኛውም ሥፍራ መነኩሴ ነኝ
ወይም ባሕታዊ ነኝ በማለት እንዳይሰብኩ ።

ለ/ ካሁን በፊት የወሰዱት የፈቃድ ወረቀት ቢኖር ከዛሬ መስከረም ፳፬ ቀን ፳፺
ዓ ም ጀምሮ የተሠረዘ መሆኑ ታውቆ ይኸንኑም የፀጥታ አስከባሪዎችና ምእመናን ሁሉ
አውቀውት ለመተባበር እንዲችሉ ውሳኔው በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ።
አውቀውት ለመተባበር እንዲችሉ ውሳኔው በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ።
ሐ/ ለወደፊቱ ግን የስብከት ፤ ፈቃድ የሚጠይቁ ቢኖሩ ለዚህ ተግባር ከተቋቋ

መው ኮሚቴ በስተቀር ሌላ ፈቃድ ሰጭ ባለሥልጣን እንዳይኖር ተደርጓል ።
መው ኮሚቴ በስተቀር ሌላ ፈቃድ ሰጭ ባለሥልጣን በተሰጣቸው ቤተ መቅ
መ/ የየአድባራቱ አለቆች የገዳም አበምኔቶች በኃላፊነት በተሰጣቸው ቤተ መቅ

ደሶች ከራሳቸውና እነርሱ ከሚጋብዙት የታወቀ መምህር ፤ በስተቀር የፈቃድ ወረቀት
ቢኖረውም በሰበካቸው ውስጥ ያለእነርሱ ፈቃድ ገብቶ ማንም ሰው እንዳይሰብክ ተከ
ልክሏል ።

ሠ/ ይህንንም የየቤተ መቅደሱ አስተዳዳሪዎች ከክፍላቸው በዘበኞችና በየአቅራ
ቢያቸው ከሚገኙት የፀጥታ ጠባቂዎች ጋር በመነጋገር እንዲያስከብሩ ፤ ይህ ውሳኔ
ከተሰጠ በኋላ በሰበካቸው ውስጥ የማይገባ ስብከት ተነግሮ ቢገኝ በኋላፊነት ተጠያ
ቂዎች መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው ።

ረ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፤ ፀጥታ አስከባሪዎች
ሁሉ ይህንኑ አውቀውት የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ለመነጣጠል የሚጥሩ አወና
ባጆችን ለማስወገድ እንዲችሉ ፤ የዚሁ ውሳኔ በሸኝ ደብዳቤ አማካይነት ይላክላቸው፤
ሲል ውሳኔ ሰጥቷል ።



# በተፈጥሮ አደጋ ድርቅ ስለደረሰባቸው ሀገሮች የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ መልእክት

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ መልእክት ፡

በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች የደረሰው ከባድ የድርቅ ችግር በማንኛውም ደረጃ ላይ ያለውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከጥልቅ ኀዘን ላይ ጥሎታል ። በዚሁ ከባድ ችግር በደረሰው ረኃብ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሕጻናትና ሽማግሌዎች ማለቃቸው ወደ ፊት በሕይወታችን የማንረሳውና በታሪካችንም ተመዝግቦ ሲያሰቅቅ የሚኖር ሰቀቀን ነው ። በተለይም ይኸው ከባድ ችግር በመገናኛ መሣሪያዎች በግልጽ እንዲታወቅ ከተደረገ ወዲህ ችግሩ የጋራ በመሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሚችለው መጠን የርዳታ ክንዱን በመዘርጋት ላይ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካሁን ቀደም በምትችለው መጠን ርዳታ አድርጋለች ። ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ያገኘነውን ገንዘብ ለዚሁ ከባድ ችግር ማቃለያ እንዲውል ለኮሚሺኑ አስረክባለች ። እንዲሁም በአንዳንድ ክፍሎች በመገኘት ድርቁ ያደረሰውን ከባድ ችግር ለማቃለል መጠነኛ ርዳታ አድርገናል ።

ነገር ግን የድርቁን ችግር ለማቃለል ከተቋቋመው የድርቅ ማስተባበሪያ ኰሚሽንና ከሌላም አቅጣጫ በሚደርሰን መረጃ መሠረት የድርቁ ችግር እየከበደና በበለጠ አስደ ናቂ እየሆነ ከመሄዱ በቀር አለመቃለሉን ለመገንዘብ ችለናል ።

ስለዚህ ይህንኑ ከባድ ችግር በተቻለ መጠን ለማቃለል በሚደረገው ጥረት ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ እንድትሆን በማሰብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኰሚሽን አማካይነት የድርቅ ማስተባበሪያ ኰሚቴ አቋቁመናል ። ይህም ኰሚቴ ከአ ገር ውስጥና ከውጭ አገር የርዳታ ውስጥና ከውጭ አገር የርዳታ ገንዘብና ሌላም ዓይነት ርዳታ እየሰበሰበ በቀጥታ ለድርቅ ማቃለያ በማዋል እንዲሠራ ከፍተኛ አደራ ተጥሎበታል ።

ለዚሁ ኰሚቴ የሚቀርበውን የመጀመሪያ ርዳታ ለማበርከት ተቀዳሚ የሆናችሁ ዕድለኞች ናችሁ ። ይህንኑ ከባድ ችግር በማቃለል ረገድ በቀጥታ ተካፋይ ሆነን ለመሥ ራት ላቋቋምነው ድርጅት መነሾ ሊሆን የሚችለውን ገንዘብ በማበርከታችሁ በበጎ አድ ራጎታችሁ ብቻ ሳይሆን በምሳሌነታችሁ ከልብ እናመሰግናችኋለን ።

ወደፊትም ቢሆን በዚሁ ረገድ ችግሩን በማሳወቅና ተጨማሪ ርዳታ ከሌሎች ለማ ግኘት በምንችልበት መንገድ ተባባሪ በመሆን እንድትረዱን አደራ እላችኋለሁ ። እግዚአብሔር ውለታችሁን ይክፈላችሁ ።

የርዳታውም ገንዘብ ማጠራቀሚያ ቁጥር 20330 አራት ኪሎ ንግድ ባንክ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የአስተዳደር ከፍተኛ ጉባኤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በእዚህ ዓመት በተለይ ቤተ ክርስ ስቲያን ስለሚኖራት ዘመናዊ የአስተዳደር አመራር በቃለ ዓዋዲ ተወስኖ ደንቡ ወጥቷል። ይህ ደንብ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከዘመናዊ የአመራር ለውጥ ጋር አብሮ እንደሚያራምዳት ፈጽሞ ታምኖበታል ፤ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ አመራርን ተከትላ መራመድ ስላለባት ይህንኑ የሚገልጸው ቃለ ዓዋዲ የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ሁለተኛ ዓመት ቊጥር ፬ በወጣው እትም ላይ ተገልጿል ።

የቃለ ዓዋዲው መግለጫ ሙሉው ቃል ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ከፍተኛ ጉባኤ ደንብ

መቅድመ ነገር ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት መካከል አስፈላጊውን አገልግሎት ከመስጠት የተቆጠበችበት ጊዜ ባይኖርም ባለፈው ጊዜ የፈጸመችውን ፤ አሁንም የምትፈጽመውንና ወደፊትም ልትሰጥ የምትችለውን አገልግሎት እንደጊዜውሁናቴ መርምሮ ለማስተካከል ፤ አበው ጠብቀው ያቆዩትንና ያስተላለፉልንን ሥርዓቷንና ትምህርቷን ስፋቷንና ምልዓቷን መርምሮ እያጠና የሚሻሻለውን እንዲሻሻል ፤ የሚጠበቀውን እንዲጠበቅ ለማድረግ ። ቤተ ክርስቲያን ከጊዜው ጋር እኩል እየተራመደች ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገንም ማገልገል የተመሠረተችበት ዓላማ በመሆኑ ፤ በዘመናዊ አስተዳደር መብቷና ግዴታዋ ተለይቶ የምትመራበትን የአስተዳደር ፤ በተለይም ካህናትና ምእመናን ኃላፊነታቸውን ተገንዝበው በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሚሳተፉበትን አቅዋም ለመትለም ሲል ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን አስተዳደር ከፍተኛ ጉባኤ አቋቁሟል ።

አንቀጽ ፩

አጭር ርእስ

ይህ ደንብ የ፲፱፻፹፯ ዓ/ም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ከፍተኛ ጉባኤ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

አንቀጽ ፪

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ከፍተኛ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ ጉባኤ እየተባለ የሚጠራው) በቅዱስ ሲኖዶስ ተቋቁሟል ።

አ ን ቀ ጽ ፫

የጉባኤው አባሎች ምርጫና ስብሰባ

፩ ፡ ጉባኤው ከቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ የተመረጡ ከአሥራ ሰባት የማያንሱ ከሃያ ሦስት የማይበልጡ አባሎች ይኖሩታል ።

፪ ፡ የጉባኤው የሥራ ጊዜ ከሁለት ዓመታት የማይበልጥ ይሆናል ፤ ሆኖም የጉባኤው መኖር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሥራው ጊዜ በቅዱስ ፓትርያርኩ ትእዛዝ ሊረዝም ይችላል ።

፫ ፡ የጉባኤው አባሎች በጽኑ እምነታቸውና በበጐ ምግባራቸው የታወቁ ካህናትና ምእመናን ሲሆኑ በበጎ ፈቃድ ስለሚሠሩ አበል አይከፈላቸውም ።

፬ ፡ ማንኛውም አባል በማናቸውም ሁናቴ የተመረጠበትን የሥራ ዘመን ሳይፈጽም ከሥራ የተሰናበተ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በቍጥር ፩ መሠረት ሌላ አባል ይመረጣል ።

፭ ፡ ከጉባኤው አባሎች ከእኩሌታው በላይ ከተገኙ ምልዓተጉባኤ ይሆናል ። ማንኛውም ጉዳይ በስብሰባው በተገኙ አባሎች ድምፅ ብልጫ ይወሰናል ፤ የተሰጠው ድምፅ እኩል ሲሆን ሊቀ መንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል ።

፮ ፡ ፓሊሲ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ለመወሰን ከአባሎች ፪/፫—ሁለት ሦስተኛው ካልተገኙ ምልዓተ ጉባኤው አይሆንም ።

፯ ፡ ጉባኤው የተጣለበትን ሥራ በሚገባ ባለማከናወን የጉባኤው ሊቀ መንበር የፓትርያርኩ እንደራሴ ይሆናል ።

ሀ/ ከአባሎቹ መካከል የሚመረጡ አንድ ም/ሊቀ መንበርና አንድ ጸሓፊ

ለ/ አንድ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ

ሐ/ አንድ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተም ጋዜጣ ይኖረዋል ።

አንቀጽ ፬

ዓላማዎች

የጉባኤው ዓላማዎች ከዚህ የሚከተሉት ይሆናሉ ።

፩ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በዘመናዊ አቅዋም የሚደራጅበትን ጥናት ማከናወንና ማስፈጸም ።

፪ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን ተከትላ ሥርዓቷን አሻሽላ ፤ ጠቅላላ አቅዋሟንና የሥራ አመራሯን የሚመለከቱ ደንቦችና የተሐድሶ ሥርዓቶችን ማዘጋጀትና በሥራ ላይ እንዲውሉ ለቅዱስ ሲኖዶስ ማቅረብ ።

፫ ፡ ምእመናን ከቤተ ክርስቲያን ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲኖራቸውና እምነታቸውን በሚገባ ተረድተው ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግ ።

፬ ፡ ካህናትና ምዕመናን በኅብረት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተካፋይ የሚሆኑበትን መንገድ መፈለግና ማዘጋጀት ።

፭ ፡ በቤተ ክርስቲያን ሥር ተቋቁመው የሚገኙትን ልዩ ልዩ ድርጅቶችና መምሪያዎች አቅዋምና ተግባር እያጠናና እየመረመረ ማስተካከል ፤ አስፈላጊ ሆኖም ከተገኘ በመሠረዝ ወይም በማጠፍ የተሻለ አቅዋም መመሥረት ።

፮ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀብት ፤የንብረትና የጥንታዊ ቅርሶቿ አቅዋም በሕግ እንዲወሰንና እንዲጠበቅ ማድረግ ።

፯ ፡ በሀገር ውስጥና በውጭም አገር ልዩ ልዩ አቅዋም ያላቸው አድባራትና ገዳማት እንዲሁም ሀብትና ንብረት በቤተ ክርስቲያን ቀጥታ ቍጥጥር ሥር እንዲሆኑና ተመሳሳይ አስተዳደር እንዲኖራቸው ማድረግ ።

፰ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥና በውጭም አገር ከሚገኙ ልዩ ልዩ እምነት ካላቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ሊኖራት የሚገባትን ግንኙነት ማጥናትና ተገቢው ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ እንዲወሰን ማድረግ ።

፱ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በስብከተ ወንጌል፡በአስተዳደር በማኅበራዊ ኑሮና በኤኮኖሚ ልትከተለው የሚገባትን አቅዋም ማጥናትና ተገቢው



www.ethiopianorthodox.org

ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ።

፲ ፡ በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉትን ካህናት አቀዋምና አስተዳደር በጥንቃቄ አጥንቶ ውሳኔ መስጠት ።

፲፩ ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ፤ ንዋየ ቅድሳት ፡ አልባሳትና የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ዕቃዎች ሁሉ በማናቸውም ግለ ሰብእ ወይም ድርጅት እንዳይሸጡና የትርፍ ማግኛ እንዳይሆኑ የሚጠበቁበትን መንገድና በቤተ ክርስቲያን ሥር የሚሆኑበትን ዘዴ አጥንቶ መወሰን ።

፲፪ ፡ ቤተ ክርስቲያን ሀገሪቱ በምታደርገው የትምህርት ፤ የማኅበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ (ምጣኔ ሀብት) ሙሉ ተሳታፊ የምትሆንበትን የልማት ሥራ ማጥናትና ማደራጀት ።

## አንቀጽ ፫

ጉባኤው በአንቀጽ ፬ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ዓላማዎች በሥራ ላይ ለማዋል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የማስፈጸም ሥልጣን ይኖሩታል ።

፩ ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሁሉ ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚጠነክርበትን መንገድ ይቀይሳል ።

፪ ፡ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር አስፈላጊ ሆነው ለተቋቋሙት መምሪያዎችና ድርጅቶች ባጀት አጥንቶ በዋናው ጸሐፊ አማካይነት ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርቦ ያስወስናል ።

፫ ፡ ለጉባኤው ተግባርና ለቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገርም በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ የሚሰበሰብበትን መንገድ ያዘጋጃል በሚገባ መጠበቁንም ያረጋግጣዋል ።

፬ ፡ የውስጥ የሥራ መመሪያውን ያወጣል ።

፭ ፡ ተጠያቂነቱ በቀጥታ ለፓትርያርኩና ለቅዱስ ሲኖዶስ ይሆናል ።

፮ ፡ የጉባኤው ተግባር እንዲቀለጥፍና ውሳኔዎቹም በሥራ ላይ እንዲውሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ ለጉባኤው ተጠያቂ እንዲሆን ከፓትርያርኩ የሥልጣን ውክልና ለጉባኤው በልዩ ትእዛዝ ይሰጠዋል ።

፯ ፡ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በሰፊው ከመረመረና ካጠና በኋላ ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲቀርብ ያደርጋል ። የአስተዳደር ጉዳይ ሲሆን ግን ውሳኔውን ቅዱስ ሲኖዶስ ተቀብሎ ባያጸድቀው በፓትርያርኩ ወይም በእንደራሴው ሊቀመንበርነት በቍጥርእኩል የሆኑ የሲኖዶሱና የጉባኤው ሥራ አስፈጻሚ አባሎች በተገኙበት ስብሰባ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል ፤ የተሰጠው ድምፅ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ የደገፈው ወገን ይጸናል ።

፰ ፡ ጉባኤው ለሥራው መቃናት የሚረዱትን የጥናት ኮሚቴዎች ማቋቋም ይችላል ።

፱ ፡ ጉባኤው ለሥራው አስፈላጊ የሚመስሉትን የቤተ ክርስቲያን ሠነዶች ለመመርመር፤ ሰዎችን ጠርቶ ለመጠየቅ ከመንግሥትም ሆነ ከግል ድርጅቶች የሒሳብ መርማሪዎችን ጋብዞ የሒሳብ ሠነዶችን ለማሥመርመር ይችላል ።

፲ ፡ ለእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በሊቀ ጳጳሱ ሊቀ መንበርነት የሚመራ ከካህናትና ከምእመናን የተመረጡ ከሰባት የማያንሱ ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ አባሎች የሚገኙበት ጉባኤ ይቋቋማል ፡ እንዲሁም ቅዱስ ፓትርያርኩ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስመከረ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ሹማምንትና ሠራተኞችን ለመሾምና ለማሰናበት ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋወር ይችላል ።



## አንቀጽ ፯

ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ቃለ ዓዋዲ) ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም

አባ ቴዎፍሎስ

የኢትዮጵያ ፓትርያርክ

ከዚህም ሌላ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ቃለ ዓዋዲ ሁለተኛ ዓመት ቍጥር ፫ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም የሰጠው ድንጋጌ በሥራ ላይ ውሏል የቃለ ዓዋዲው ሙሉ ቃል ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፩/፲፱፻፹፯ ዓ/ም ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በ፲፱፻፹፰ ዓ/ም ተሻሽሎ በቍጥር ፹፫/፹፰ በወጣው ትእዛዝ መሠረት ፤

# የ ወ ጣ   ደ ን ብ

፩ ፡ ይህ ደንብ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በቍጥር ፹፫/፲፱፻፹፰ ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው ትእዛዝ በአንቀጽ ፪/፩/፫ እና በአንቀጽ ፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በቤተ ክህነት ጉባኤ አማካይነት ፓትርያርኩ ያወጣው ደንብ ነው ።

፪ ፡ ይህ ደንብ «ስለዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በቍጥር ፫፻፷፬/፲፱፻፷፩ ዓ/ም የወጣውን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ደንብ ለማሻሻል የወጣ የ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፫ ፡ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፫፻፷፬/፲፱፻፷፩ አንቀጾች ፫ እና ፬ ተሠርዘው በሚከተለው ማሻሻያ ተተክተዋል ።

፫ ፡ በቤተ ክህነቱ ጉባኤና በፓትርያርኩ መሪነትና ቍጥጥር ሥር ሆኖ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ዋና ኃላፊ የሚሆን በጉባኤው (በሲኖዶስ) አቅራቢነት በፓትርያርኩ የሚሾም አንድ ዋና ጸሐፊ ይኖራል ።

፬ ፡ ዋና ጸሐፊው ከላይ በተመለከተው ሳይወሰን ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ይፈጽማል ።

፩ ፡ የጠ/ጽ/ቤቱን የልዩ ልዩ ክፍሎችና ዘርፎች መሥሪያ ቤቶችን አስተዳደር ይመራል

፪ ፡ ከቤተ ክህነት ጉባኤ(ቅዱስሲኖዶስ) የሚወሰኑት ውሣኔዎችና መመሪያዎችፍጻሜ እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

፫ ፡ የቤተ ክርስቲያን ገቢ እንዲሰበሰብ ያደርጋል ፤ መሰብሰቡንም ያረጋግጣል ፤

፬ ፡ የቤተ ክህነትን ጉባኤ (ሲኖዶስ) አስፈቅዶ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ፤

፭ ፡ የቤተ ክህነትን ጉባኤ አስፈቅዶ የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረትን አሲዞ ገንዘብ ለመበደር ፤

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ ከቤተ ክህነት ጉባኤ ጋር በመመካከርና በማስፈቀድ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለተወሰነ ጊዜ ለመከራየትና ለማከራየት ፤

፯ ፡ የቤተ ክርስቲያንን ጥንታውያን ንብረቶች መሸጥ ፤ መለወጥ ወይም ማስያዝ ካል ሆነ በቀር በቤተ ክህነት ጉባኤ ፈቃድ ማንኛውንም ውል ለመዋዋል ፤

፰ ፡ ከቤተ ክርስቲያን አቋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎችን በማካሄድና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት የስብከትና ያገልግሎት ዓላማ የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሚለማበትን ጥቅም የሚያስገኝበትን ዘዴ እያጠና ከሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ለቤተ ክህነት ጉባኤ ያቀርባል ።

፱ ፡ የዕለት ሥራ አመራርን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስም አስፈላጊውን ይፈጽማል ፤

፲ ፡ የቤተ ክርስቲያን የሒሳብና የንብረት መዛግብትማኅደር ጉዳዮች በሚገባ እንዲጠበቁ ያደርጋል ፤

፲፩ ፡ የቤተ ክርስቲያንን መ/ቤቶች የሥራ አመራርና የገንዘብ አስተዳደር ይመራል ፤ ይቈጣጠራልም ፤

፲፪ ፡ በየዓመቱ ከጥቅምት ወር መጨረሻ በፊት ባለፈው ዓመት ውስጥ በርሱና በቤተ ክህነት ጠ/ጽ/ቤት የተፈጸሙትን ሥራዎች በዝርዝር የሚያስረዳ ዓመታዊ መግለጫ ለቤተ ክህነት ጉባኤ ያቀርባል ፤

፲፫ ፡ የቤተ ክህነትን ጠቅላላ የዓመት በጀት አዘጋጅቶ በየዓመቱ ከሰኔ ፴ ቀን በፊት ለቤተ ክህነቱ ጉባኤ (ሲኖዶሱ) አቅርቦ ያስፈቅዳል ።

፲፬ ፡ በተፈቀደው በጀት መሠረት ማንኛውም ወጭ የሚደረገው በእርሱ ፊርማ ሆኖ በሌላ ጊዜ ግን በርሱ አማማቢነት በፓትርያርኩ ወይም እንደራሴው በሚወከለው ባለሥልጣን ፊርማ መሆኑን ያረጋግጣል ፤

፲፭ ፡ ለቤተ ክህነት መልካም አመራርና ለቤተ ክርስቲያን ዓላማዎች ፡ ተግባሮችና አገልግሎቶች ዕድገትና ፍጻሜ ማግኘት አስፈላጊ የሆኑትን ሐሳቦች እያጠናና እያስጠና በየጊዜው ለቤተ ክህነት ጉባኤ ሐሣብ ያቀርባል ፤

፲፮ ፡ ስለ ቤተ ክህነት ጠ/ጽ/ቤትና ዘርፎች መሥሪያ ቤቶች አቋም ዝርዝር ተግባርና ግንኙነት አጥንቶ የውስጥ ደንብ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ክፍል ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ደንብ አጥንቶ ለቤተ ክህነት ጉባኤ ሊያቀርብ ይችላል ፤

፲፯ ፡ በማንኛውም የክስ ጉዳይ ስለ ቤተ ክህነት በመወከል ይቀርባል ወይም የቤተ ክህነት ጉባኤን አስፈቅዶ ሌላ ሰው ይወክላል ፤

፲፰ ፡ ከዚህም ሌላ የቤተ ክህነት ጉባኤ (ቅዱስ ሲኖዶስ) የሚወስንለትን ሌላም ተግባር ሁሉ ይፈጽማል ።

፳ ፡ ይህ ደንብ በቃለ ዓዋዲ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም
አባ ቴዎፍሎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ



የቅዱስነታቸው ታላቅ መንፈሳዊ ተግባር በመመጠን የቦስቶን ዩኒበርሲቲ የክብር ዲግሪ ሰጥቷቸዋል



www.ethiopianorthodox.org



ፓትርያርኩ በመንበረ ፓትርያርካቸው አንዳንድ መንፈሳዊ ተግባሮችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከመንፈሳውያን አባቶች ጋር እየተገኙ ሲወያዩ



ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያን ገዳም ሲመለከቱና መግለጫ ዎችን ሲያዳምጡ



[illegible] በየክፍለ ሀገሩ በመዘዋወር አቋቁመዋል

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዓለም ፊት ለማሳወቅ ፓትርያርኩ ያልተቆጠበ

# ጥረት አድርገዋል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም የመንፈሳዊ ታሪክ ውስጥ ጥንትም የታወቀ ዝና ይኑራት እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሥፍራ እንድታገኝ የተደረገው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በአደረጉት ያልተቆጠበ ጥረት ላይ የተመሠረተ ነው ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረቱት አባል ሀገሮች ቀደምትነት ሥፍራ በመያዝ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት በኩል የአላት ክብር የላቀ ነው ።

የዓለም ክርስቲያኖች በመተባበርና በመደጋገፍ አንድ ሆነው ስለ ክርስቶስ መንግሥት ስለ ሰብአዊ ልጅነት ክብር ስለሰው እኩልነት ማኅበራዊ ዓላማን በመሥራት ቆርጠው የተነሡበት ጊዜው ምንም ብዙ ዘመናትን ያስቈጥር እንጅ በሐሳብ በመለያየት፣በሥልጣን በመከፋፈል ብዙ ጊዜ ችግር እየደረሰ የኀብረቱ ነገር ሲወድቅና ሲነሣ ኖሯል ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ከተመሠረተ በኋላ ግን የክርስትና ዓላማ መሠረተ ይዞታ በትክክል አቅጣጫውን ይዞ እንዲራመድ በማድረግ የጋራ ጥረት በመደረጉ ዛሬ በዓለም የአሉ ክርስቲያኖች ርስ በርስ በመረዳዳት ምግባረ ሠናይ በመፈጸም ለተቸገረው የዓለም ሕዝብ እንደ ድርቅ ጎርፍና እነዚህንም የመሳሰሉ አደጋዎች ሲደርሱ ርዳታ በማድረግ እጁን ይዘረጋል ።

በልማት ወደኋላ ለቀሩት ሀገሮችም በልማት የተራመዱት ክፍሎች እየተሳሰቡ የገንዘብ የትምህርት የጤና ፣ ወዘተ መስፋፋት በየሀገሩ እንዲዳረስ ብዙ ጥረት ያደረገና ወደ ፊትም በእዚሁ ይዞታ እየቀጠለ የሚሄድ ድርጅት ነው ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረቱት መንፈሳውያን መሪዎች መካከል አንዱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ መሆናቸውን ይኸው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታሪካዊ መዝገብ ያረጋግጣል ።


ከእዚያም በኋላ ብፁዕነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን በዘመናዊ ርምጃ ከፍ ያለ ቦታ እንድታገኝ በአደረጉት ጥረት በአሁኑ ጊዜ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ርዳታ የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ማስፋፊያ ድርጅት ይገኛል ። ይህ ኮሚሽን ካህናትን በማሠልጠን ርሻዎችን በማስፋፋት ሥነ ጽሑፎችን ለማራባትና እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ሥራዎች ሁሉ ፍሬ እንዲያገኙ የሚጥር ክፍል ነው ።

ከእዚህም በቀር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በኩል የሕክምና መስጫ ድርጅት እንዲቋቋም ያደረገችው ትግል ግብ ሳያገኝ የቀረ አይደለም ውጤት የተገኘለትና ፍሬ የያዘ ሆኗል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመሻሻል መፍትሔን ለመፍጠር ገና በእንደራሴነታቸው ጊዜ ጀምሮ ጥረት ያደርጉ ስለነበር ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲሉ ልዩ ልዩ ሀገሮችን በመጎብኘት እየተነጋገሩ ከፍጻሜ አድርሰዋል ።



ቅዱስነታቸው የኢየሩሳሌምን ቅዱስ መካን እየተዘዋወሩ ሲመለከቱ።



ቅዱስ ፓትርያርኩ በሀገር ውስጥ በመዘዋወር አንዳንድ መንፈሳውያን ጉብኝትን ሲያከናውኑ

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተማሪዎችም በእዚህ በኩል የትምህርት መስክ ስላገኙ ወደ ውጭ ሀገር እየተላኩ ዛሬ ሀገሪቱ የምትፈልጋቸውን ምሁራን በመጠኑም ቢሆን ለማስገኘት ተችሏል ።

ይልቁንም በብፁዕ ፓትርያርኩ አሳቢነት ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ አብያተ ክርስቲያን አባል በመሆን ስለሰላም ለሚደረገው ጥረት ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ተካፋይ በመሆን ሰፊ ግልጋሎት ሰጥታለች ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የቤተ ክርስቲያኒቱን የወደፊት ዕድል በመገንባት ከአደረጉት ልዩ ልዩ የውጭ ሀገር ጉብኝት ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያንን በመጋበዝ በ፲፱፻፷፱ዓ፡ም፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ደርግ በኢትዮጵያ ላይ ተደርጓል በእዚሁ ዓመት በነሐሴ ወር ደግሞ እነዚሁ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ምሁራን አዲስ አበባ ላይ ተሰብስበው በልዩ ልዩ ዐበይት መንፈሳውያን ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል ።

ይህም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መሻሻልና ዘመናዊ አመራር ዓይነተኛ መፍትሔ ነው ይህ ዓይነት መንፈሳዊ ስብሰባ በአንድ ሀገር በሚካሔድበት ጊዜ ልኡካኑ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ለመረዳትና ለማወቅ ያስችላቸዋል ። አንዳንድ የሐሳብ ልዩነትም ቢኖሩ እንኳን እነዚህኑ ልዩነቶች በማቀራረብና በማስማማት ረገድ ይህ ዓይነት ጉባኤ መድኅን ይሆናል ።

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ ልትከተለው የሚገባው መንገድ እንደቀድሞው በአጭር ብቻ በመወሰን ሳይሆን ግንኙነቷን በማስፋፋት ከመላው ዓለም ጋር መንፈሳዊ መተባበርን ጭምር ያጠቃልላል ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗን በማስተማር በማስተባበር በምእመናኗ ድጋፍና መተባበር የምትራመድበት ጊዜ ነው ።

ይህም አድራጎት የቤተ ክርስቲያንን የሥራ እንቅስቃሴ በይበልጥ ያራምደዋል ማንም ሰው ቢሆን ሥርተህ ግረህ ጥረህ በላብህ ወዝ ብላ ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ራሷ ቤተ ክርስቲያኗ የትእዛዙ መሠረት መሆን ይገባታል ። ቤተ ክርስቲያን በልማትጐን ተሰልፋ የምትሠራበት እንደሌሎቹ ዓለማት የሕክምና አዋቂዎች አስተምራ ሕዝቡን በመርዳትና በጤናውም በኩል እንክብካቤ በማድረግ ጭምር በነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት የተቀደሱ ተግባሮች ላይ ለመሠማራት የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የማይቆጠብ ፍላጎት በመሆኑ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባል ቤተ ክርስቲያናችንን በመተባበር እንድንደግፍ ያስፈልጋል በመለያየትና በመጠላላት በሐሳብ አለመግባባት የምንራመድ ከሆንን ለቤተ ክርስቲያናችን ፈጣን የሥራ እንቅስቃሴ ጐታቾች እንሆናለን ይህ ግብር የአለባቸው ሁሉ በእውነተኛ ቅደስና አስተሳሰብ ላይ ሐሳባቸውን በመለወጥ መንፈሳዊ ተራማጅ እንዲሆኑ ያስፈልጋል ።

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ በኅብረተ ሰብአዊነት አመራር በምትራመድበት ወቅት የምትፈልገው መተባበርንና አንድ ሆኖ ስለሕዝብ ሲሉ ያለዕረፍት ጠንክሮ መሥራትን ነው ። ስንፍና የሐሳብ ልዩነት የርስ በርስ የተንኮልና የምቀኝነት መጠላላት ግን ለኅብረተ ሰብአዊነት አስተዳደር ፍጹም እንቅፋት ስለሚሆን ክፉውን ትተን በጐ ምግባርን እንከተል ።



# የፓትርያርኩ ስጦታ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ለደብረ ገነት ኤልያስ እና ለመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆን ንብረት ፈቅደው ሰጥተዋል ይኸው የቅዱስነታቸው ሙሉ ቃለ ኑዛዜ ቀጥሎ የተመለከተው ነው ፤

## ቃ ለ ኑ ዛ ዜ ።

በአዲስ አበባ ከተማ በብሔራዊ ስታዲየም በስተጀርባ የሚገኘውን በቊጥር ካርታ የተነሣውን ቦታየንና በላዩም ላይ ያሠራሁትን ፎቅ ቤትና የመኪና መቋሚያ ቤቱን ጭምር በሥጋ ብቻ የተወለድሁበት ሳይሆን በጥምቀትም ከሥላሴ ለተወለድሁበትና ከሰፊውም የመንፈሳዊ ትምህርት ገበታ በመጀመሪያ ለተሳተፍሁበት በጐጃም ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ለሚገኘው ለደብረ ገነት ኤልያስቤተክርስቲያንና የሕይወቴን ዘመን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዳውል ለመረጠኝ አምላክ መመስገኛ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ በአዲስ አበባ በጉፋ ሠፈር አጠገብ በግል ገንዘቤ በገዛሁት ቦታ ላይ ላቋቋምሁት ለመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ርስት አድርጌ በዚህ ጽሑፍ ሰጥቻለሁ ።

## የስጦታውም ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል ።

፩ኛ/ ቤቱን ያሠራሁት ከባንክ በወለድ ተበድሬ ስለሆነ የብድሩ ገንዘብ ከነወለዱ በሙሉ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ የኪራዩ ገቢ ለዕዳው ይከፈላል ።

፪ኛ/ የባንኩም ዕዳ ተከፍሎ ሲያልቅ የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ ከፍጻሜ እስኪደርስ ድረስ ቤቱ የሚያስገኘው ገቢ በሙሉ ለዚሁ ሕንጻ ማስፈጸሚያ ይሆናል ።

፫ኛ/ ዕዳው ከነወለዱ ከተከፈለና የተባለውም ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራ ከፍጻሜ ከደረሰ በኋላ ፤ ቤቱ የሚያስገኘው ገቢ ከሁለት ተከፍሎ እኩሌታው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን፤ እኩሌታው ደግሞ በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስም በሚከፈትሒሳብ በባንክ እየተቀመጠ ፤ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ለሚከተሉት ጉዳዮች ወጭ እየሆነ ይሠራበታል ።

፩/ (ሀ) ከደብረ ገነት ኤልያስ ድርሻ እኩሌታው ወለድ በሚያስገኝሒሳብ ውስጥ በባንክ እየተቀመጠ ፤ ለሕንጻው ማደሻና መጠገኛ ይሁን ።

(ለ) እኩሌታው ደግሞ ለሁለት ተከፍሎ ፤ አንዱ እጅ ለዜማ ፤ ለቅኔ ፤ ለቅዳሴና ፤ ለመጻሕፍት ትርጓሜ መምህራን ደመወዝ ፤ ይዋል ።

አንዱ እጅ ሰዓታት ስብሐተ ነግሕና ማኅሌት ለሚቆሙ ቅዳሴ በመቀደስ ለሚያገለግሉ ካህናት ይሰጥ ።

፪/ (ሀ) እንደዚሁም ከመካነ ሕያዋን ቤተ ክርስቲያን ድርሻ እኩሌታው ለቤተ ክርስቲያኑና ለትምህርት ቤቱ ሕንጻ ማደሻና መጠባበቂያ ይሁን ።

(ለ) እኩሌታው ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን ለሚያገለግሉ ካህናትና በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ በተቋቋመው ት/ቤት ለሚያስተምሩ አስተማሪዎች ይዋል ።

፫ኛ/ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠውን ንብረት በውክልና የመጠበቅና

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በግል ገንዘባቸው ያሣነፁት የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይህ ነው ።

የኪራዩም ገቢ በጊዜው እየሰበሰበ በያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ስም እባንክ የማስቀመጡ አላፊነት በደብረ ገነት ኤልያስ ደብር አስተዳዳሪ በድማኅ ገነቱና በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በሁለቱ በሚመረጥ በአዲስ አበባ ተቀማጭ ለሆነ ሰው ይሰጣል ። አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ በሁለቱ አስተዳዳሪዎች በሚወሰነው መጠን ከገቢው አበል ሊከፈለው ይችላል ።

፩ኛ/ (ሀ) የደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ የሆነው ገቢ በደብሩ አስተ ዳዳሪ በድማኅ ገነቱ ሰብሳቢነት በማኅበሩ የሚመረጡ ሁለት ሰዎች በአባልነት በሚገ ኙበት ኮሚቴ ከተመከረበት በኋላ በአንድ ቃል ወይም በድምፅ ብልጫ በሚስማሙ በት መሠረት ሦስቱም የፈረሙበት ቃለ ጉባኤ በደብሩ ጸሐፊ እጅ በሚገባ እየተቀመጠ ፤ ከዚህ በላይ ለተመለከቱት ጉዳዮች ድልድሉ ሳይፋለስ በድማኅ ገነቱ ፊርማ ከባንክ ወጭ እየሆነ ይሠራበት ።

(ለ) በቤተ ክርስቲያኑ ድርሻ ሀብት ክርክር የተነሣ እንደሆነ ፤ የጐጃም ሊቀ ጳጳስ በጉባኤ አይቶ በሚወስነው መሠረት ይፈጸም ።

፪ኛ/ (ሀ) የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ድርሻ የሆነው ገቢ በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ሰብሳቢነት ከማኅበሩ በሚመረጡ ሁለት ሰዎች በአባልነት በሚ ገኙበት ኮሚቴ ከተመከረበት በኋላ ባንድ ቃል ወይም በድምፅ ብልጫ በሚስማሙበት መሠረት ሦስቱም የፈረሙበት ቃለ ጉባኤ በቤተ ክርስቲያኑ ጸሐፊ እጅ በሚገባ እየተ ቀመጠ ፤ ከዚህ በላይ ለተመለከቱት ጉዳዮች ድልድሉ ሳይፋለስ በቤተ ክርስቲያኑ አስ ተዳዳሪ ፊርማ ከባንክ ወጭ እየሆነ ይሠራበት ።

## ቅዱስ ፓትርያርኩ ያሠሩት የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ቅዱስፓትርያርኩ ያሠሩት የመካነ ሕያዋን ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ።


እሁድ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ብፁዕ ወቅ/አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በግል ገንዘባቸው ያሳነጹት የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሥራው ተጠናቅቆ ስለተፈጸመ በእዚሁ ዕለት በቅዱስነታቸው ተባርኮ ታቦቱ ከመቃ ኞው ወጥቶ እጅግ አምሮና ተውቦ ወደተሠራው ታላቅ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ውስጥ ገብቷል ።

ዑደት ተደርጎ ታቦቱ ከዓውደ ምሕረቱ ላይ እንደ ቆመ አለቃ አያሌው ታምሩ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረትና ስለ ታቦት ስለ ጻድቃንና ሰማዕታት ስለ መላእክት አማ ላጅነት ሰፋ ያለ ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ቤተክርስቲያኑን ለመሥራት እንዴት እንዳሰቡና ያሰቡትም ሐሳብ በሥራ ላይ ውሎ ከፍጻሜ ደርሶ በማየታቸው የተደሰቱ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ በቦታው ለተገኙት ምእመናን ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል ። በመጨረሻም ቡራኬ ከሰጡ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

በበዓሉ ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የአድባራት አለቆችና በርከት ያሉ ምእመናን ተገኝተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org



ፓትርያርኩ በአካል የደከሙትን ለማጽናናት በየቦታው እየተገኙ መንፈሳዊ ምክር ሰጥተዋል ።



# የልማት ኮሚሽን አመሠራረት

በሐምሌ ወር ፲፱፻፷ ዓ ም ኡፕሳላ ላይ ተሰብስቦ የነበረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ ይህንኑ ጉዳይ ካወሳው በኋላ በተገለጸው መልእክቱ «ሰላምን በመፈለግ በረኃብም በመገረፍ እንጀራና ፍትሕ በማጣት በልዩነትና በደረጃ ዝቅተኛነት በመታየታቸው ሰብአዊነታቸውን ስለ መገፈፋቸው የተሰማውን ድምፅ አዳመጠን» ካለ በኋላ በባለጸጎችና በድሆች መካከል እያደገ የሚሄደውን ልዩነት ጥንቃቄ የተመላበት ውሳኔ ያስፈልገዋል ሲል ገለጸ ።

ከዚህ በኋላ ተሰብስቦ የነበረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስለአብያተ ክርስቲያናት ገንዘብ ለልማት ጉዳይ መዋል ለጠቅላላው ማኅበር ሐሳብ ለሚያቀርብ አንድ የምክክር ጉባኤ እንዲዘጋጅ ስለወሰነ ይኸው ስብሰባ በጥር ወር ፲፱፻፷፪ ዓ ም ሞንትሮ ላይ ተደረገ ። በየካቲት ወር ፲፱፻፷፪ ዓ ም የተሰበሰበው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የዚህን የምክክር ጉባኤ መግለጫና ውሳኔ በመቀበል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የልማት ኮሚሽን እንዲቋቋም ወሰነ ።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ሞንትሮ ላይ በተደረገው የቤተ ክርስቲያን በልማት ተካፋይነት የምክክር ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በመወከል የተገኙት መልእክተኛ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የልማት ኮሚሽነሮች ጉባኤ አባል ሆነው ስለተመረጡ በእሳቸው አሳሳቢነትና በአብያተ ክርስቲያናት አዘጋጅነት በጥር ወር ፲፱፻፷፫ ዓ ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በልማት ተካፋይነት በሚል ርእስ የምክክር ጉባኤ በአዲስ አበባ ላይ ተደረገ ።

በዚህ ውይይት ተካፋይ የነበሩት ፴፪ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህም ከቤተ ክህነት ፤ ከብሔራዊ ዩኒቨርስቲ ፤ ከትምህርት ምኒስቴር ፤ ከሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ፤ ከፕላን ምኒስቴር ፤ ከአዲስ አበባ ባንክ ፤ ከመሬት ይዞታ ሚኒስቴር ፤ ከሌሎቹም መንግሥታዊ ድርጅትና መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ነበሩ ።

ጉባኤው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብሔራዊ ልማት ረገድ ከፍተኛ ሥፍራ ልትይዝ እንደምትችል የሚያምንበትና ተስፋም የሚያደርግ መሆኑን ከአስገነዘበ በኋላ በተለይ ደግሞ (ሀ) በትምህርት (ለ) በብሔራዊ ፊደል ሠራዊት ፖሮግራም ፤ (ሐ) በጤና ጥበቃ (መ) በርሻና በኢንዱስትሪ በኩል ከካህናት መካከል ለአንዳንዶቹ መጠነኛ ትምህርት በመስጠት ሕዝቡን እንዲመክሩና እንዲያስተምሩ በማድረግ ሰፊ አገልግሎት ለመስጠት የምትችል መሆኗን አስገንዝቦ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን እንዲቋቋም ውሳኔዎችን አስተላለፈ ።

በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ ከታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ራሱን የቻለ በመሆን ተቋቋመ ።

የኮሚሽኑ ዓላማ ችግረኞች ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩበትን ወጣቶች በሙያ ትምህርት ሰልጥነው ከአገራቸው የበለጠ ጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ መፈለግና ሀገሪቱ በምታደርገው የትምህርት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ጥረት ተካፋይ መሆን ነው ።

ይህ የልማት ኮሚሽን በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተመርጦ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሚሾመው ሊቀ መንበርነት የሚመራ ዘጠኝ አባሎች የሚገኙበት የበላይ ኮሚቴ አለው ።



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ዓላማም ፲፩ሺህ የሚ
ሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት ድርጅቶችን አሟልቶ የልማት ጣቢያ ለማድረግና ፪፻ሺ
የሚሆኑትን ካህናት የልማት ሠራተኞች ጭምር እንዲሆኑ ለማሠልጠን ነው ።
የእቅዱም ዓላማ የመጀመሪያው ተግባር አሁን በየቤተ ክርስቲያኑ በመስጠት ላይ
ያለውን የትምህርት ደረጃ ማሻሻልና መልክ ማስያዝ ነው ።

በነዚህም ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የቀለም ትምህርት ደረጃ አቅማቸው እስከ
ሚፈቅደው ድረስ ሆኖ በኋላም ገንዘብ በተገኘ ጊዜ የትምህርት ደረጃቸውን ክፍል ከፍ
ለማድረግ የታቀደ የሥራ መስክ መኖሩን ፕሮግራሙ ያመለክታል ።

በተጨማሪም በነዚህም ትምህርት ቤቶች የሚማሩት ተማሪዎች በኑሮአቸው የሚ
ጠቅሙ አቸውንና የሚአስፈልጓቸውን እንደእርሻ ፤ እንደከብት እርባታ ፤ የጤና ጥበ
ቃና በኅብረት ሥራን የማካሄድ ትምህርቶች አብረው ይሰጡአቸዋል ።

ካህናቱ በሥራ ቀን መሬታቸውን አርሰው በወዛቸው የሚያድሩ በበዓላት ቀን ቤተ
ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ስለሆኑ ርሻ ለካህናት ከዕለት ተግባራቸው አንዱ ነው ።
ስለሆነም የጥቂት ወራት የርሻ ትምህርትና አስፈላጊው ድጋፍ ቢሰጣቸው ለአካባቢ
ያቸው ምሳሌና መምህር የሚሆኑ ምርጥ ገበሬዎች ሊሆኑ ይችላሉ ካህናትን በዘመናዊ
የርሻ ዘዴ ማሰልጠንና ከሥራ ላይ ማዋል ገበሬው በቀላሉና በቶሎ እንዲቀበለውና
እንዲሠራበት ለማድረግ ይቻላል ።

በጤና አጠባበቅም ረገድ የሕዝቡ ጤናና የአካባቢውንም ንጽህና እንዲጠብቅ
ትምህርት ከተሰጣቸው ከፍተኛ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ ።
በዚህ መሠረት የልማት ኮሚሽን አቅሙ በሚፈቅድለት ሁኔታ ባለፉት ዓመታት
ከአሥራ አራቱ ክፍላተ አህጉር የተውጣጡ ካህናት ለስድስት ወራት በልዩ ልዩ ሙያ
ነክ ትምህርቶች አሠልጥኖ ወደየመጡበት ተመልሰው የተማሩትን ትምህርት በሥራ
ላይ በማዋል ላይ ናቸው ።

አሁንም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ትም
ህርት ቤት ከአሥራ አራቱ ክፍለ ሀገር የተውጣጡ ቊጥራቸው በርከት ያሉ ካህናት በልዩ
ልዩ ሙያ ነክ ትምህርት በመሰልጠን ላይ ይገኛሉ እነዚህም የተመደበላቸውን ትምህርት
ሲጨርሱ ወደየመጡበት ክፍለ ሀገር ተመልሰው የተማሩትን ትምህርት ከሥራ ላይ
እንደሚያውሉት በታላቅ ጉጉት ይጠበቃል ።

በመሠረቱ ኮሚሽኑ የሚሰብከው የልማት ወንጌል ያልተማረው ይማር ዘንድ የተ
ቸገረው የተራበው ከችግሩ ከረኃቡ ያርፍ ዘንድ ሀገር ይለማ ዘንድ ሁሉም የተሻለ ኑሮ
ይኖር ዘንድ መሥራት መተባበርና መረዳዳት እንዲኖር ማስተባበርና ማበረታታት ነው ።

# የሊቃውንት አስተያየት በኅብረት

## ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ

ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትጠብቃት ዘንድ ከደግ ቤተ
ሰብ እንደ ኤርምያስ በማኅፀን በመንፈስ ቅዱስ ተልዕኮ ተመርጠው እናት ቤተ ክርስቲ
ያን ኀሊብ ትምህርቷን እየመገበችዎ በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓቷ ሠርታ ቀጥታ ስላሳደገ
ችዎ ብርዕ ቅጥቁጥ ኢይሰብር ፤ ከእግርዎ ጭምትነት የተነሣ አስኳሉ የወጣለት የእን
ቁላል ቅርፊት አይደቅብዎም ።

ወሡዕነ ዘይጠይስ አይጠፍዕ ከቃልዎም ልዝብነት የተነሣ የሚጠያጢያስ የጧፍ
ኩስታሪ አይጠፋበትም እስከ ይገብዕ ፍትሐ መዊአቱ ወበስመ ዚአሁ ይትአመኑ
አሸናፊ ፍርዱ በተቀዋሚዎቹ ላይ እስኪመለስና እነርሱም በሥልጣኑ እስከሚያምኑ
ድረስ ማቴ ፥ ፲፪ ፥ ፳ ፥ ፳፩ ። እንዳለው በመንፈስ ሄደ በኃይለ ኤልያስ ተራመደ ይህም ብቻ
አልበቃውም በዚህም አልተመለስም መንፈሰ አእምሮው የዕውቀት ማኅደር የጥበብ
መንበር ሆኖ የተዘጋጀ በመሆኑ ጊዜ የወለደውን ዘመን የወደደውን ዘመናዊ ዕውቀትና
ሳይንሳዊ ትምህርት ተከታትሎ መልካም ውጤትን ያስገኘ በመሆኑ በኢትዮጵያ ቤተ
ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም አዋቂዎች ዘንድ አድናቆትን ያተረፉ
አባት ናቸው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችንም መንፈሳዊውን ከዘመናዊ ዘመናዊውን ከመንፈሳዊ እንደ
ነፍስና እንደ ሥጋ አገናዝበውና አዋሕደው ትሩፋ ምግባር ወገድል ማለት በግብርም በክ
ብርም ትሩፋት የተፈጸመላቸው ተነጻጻሪና ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው አባት በመሆናቸው
መሠረተ ሕይወት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአዳም ተስፋ እን
ድትሆን በተሰጠችበት ግንቦት አንድ ቀን ለመንፈሳዊውም ሆነ ለሥጋዊው ማዕረግ
የመጨረሻ ቁንጮ ለሆነው ሢመተ ፓትርያርክ አድኗቸው እነሆ ከዚያም በፊት ሆነ ከዚ
ያም ወዲህ ለቤተ ክርስቲያን ከታች መሠረት ከላይም ጠፈር ሆነው በቅድስናቸው በን
ጽሕናቸው በትዕግሥታቸው መንጋውን በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ ።

አንተ መሠረት ነህ ባንተም መሠረትነት ቤተ ክርስቲያኔን አንጻለሁ ኢጋንንትንም
አያናውጻትም ተብሎ የተነገረው አምላካዊ ትንቢቱ በቅዱስነታቸው ተፈጽሞ በቅድስት
ቤተ ክርስቲያን ላይ የተመሠረተውን የቅዱስነታቸው መንፈሰ ልዕልና ዝናማት ዘንመው
ከተወሰነላቸው ክልል በላይ ያለልክ አልፈው እየፈነጩ ቢጐርፉ ነፋሳት ነፍሰው አዉ
ራውን ትቢያውን ቢገፍፉ ቅጠል ቢያራግፉ ማናወጽና መግፋት ማንቀሳቀስ እንኳ አይ
ሆንላቸውም ።

ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ሐዋርያው እንዳለው «ሞኝነት ካለው ምርመራና
ከትውልዶች ታሪክ ከክርክርም ስለሕግም ከሚሆን ጠብ ራቅ ከማይጠቅሙና ከንቱዎች
ናቸውና ። መለያየትን የሚያነሣ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን
እንዲያደርግ አውቀህ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሠፅኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል
ሰው ራቅ» በሚለው መንፈሳዊ መመሪያ ቅዱስነታቸው በመጠቀማቸው ለዚህ ለታላቅ
ክብር እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ አብቅቶአቸዋል ።

እርግጥ ነው አባቶቻችን ቅድስና ንጽሕና የበለጠ ሊቅነት እያላቸው ይህን ክብር ተመ
ኙት እንጂ ማግኘት አልተቻላቸውም ። «እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ ከቴዎ

www.ethiopianorthodox.org

ፍሎስ በቀር ይህችን ክብር ማንም ለራሱ ገንዘብ አድርጎ የሚወስድ የለም ። ዕብ ፭ ፡ ፬ ። ክፍ ብሎ እንደ ባለው መሠረት ይህ ታላቅ ዕድልና ክብር ለብፁዕነታቸው ብቻ ተሰጠ ። እንደ የሴፍ ተገለጠው ይህን ዕድል አባቶቻችን አላገኙትም ያልነውን እናስታውስና እንደ የሴፍ ወይም እንደ ክፉ አድራጊ ሆኖ በግብ ጳጳሳዊን የእምነት ጭቆና ሥር ለብዙ ዘመናት ታፍኖ (ታስሮ) ወይም እንደ ባህር ቀመም ለሥጋዊ ጥቅም ይቸረቸር የነበረው መንፈሳዊ ሥል ጣን የጊዜው ጊዜ ከምድረ ኢትዮጵያ በቅሎና ለምልሞ ፍሬ ጽድቁን ለመጀመሪያ ዜጊ ለቅዱስነታቸው በመታደሉ ብቻ ስለሆነ ነው ።
በዚህም ምክንያት ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ አሰኝቶአቸዋል ።

ይህም አስደናቂ ዕድል ሊገኝ የቻለበት ትንቢቱን ሲመለከት መሆኑ ነው ። ትንቢቱም እንዲህ ይላል ወአንስ ፈነውኩክሙ ከመ ትዕርሩ በዘኢጻመውክሙ ዘባዕድ ጻሙወ ሉላው አንትሙ ትባኡ ውስተ ጻማሆሙ ለእልክቱ እኔስ እናንተ ያልደከማችሁበትን ሌላው የደከመበትን ልትሰበስቡ ላክኋችሁ እነዚያ በደከሙበት እናንተ ትገቡ ዘንድ ። ዮሐ ፬ ፡ ፴፰ በማለት ያጠይቀናልና ነው ።

በዚች ዕለት ማለት ግንቦት ፩ ቀን የአዳም ተስፋ የሆነችው የቅድስት ድንግል ማርያም ሕይወት የተመሠረተበት እንደሆነ ሁሉ በዚችም ዕለት የመንፈሳዊ ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ ነፃነት ስለተገኘ ይህች ዕለት የተቀደሰች ትሁን ።



www.ethiopianorthodox.org

<u>መ ወ ድ ስ ቅ ኔ</u>

<u>ከፈንታ አበበ</u> (በዓታ ት/ቤት)

ሊቀ ምሉዓን ቅዱስ መንፈስ አእምሮ ሐዋርያቲሁ ለወልድ ቴዎፍሎስ
ሐዋርያ

አሰሰልከ ሀጉለ ምክረ ሐናንያ
በሐዳስ ሕገ ተፋቀሮ ዘበጽሐት ሮምያ
አምጣነ ብፁዓት አዕይንቲከ ድንጋሌ ወንጽሕ እለ ኀቡዓተ ይሬእያ
ትብልሂ ውስተ አፉየ እንተ አልባቲ ጉህሊያ
ኢቦአ ተናፍቆ ሥጋ መቅድንዮስ ሐራውያ
ወያስተብርካ ደርገ ለገጸ ዳዊት ልያ
በርሳቤህ ልሳንከ ወቃልከ አቢግያ

<u>ሁለተኛ</u>

አብደርከ ትሕምም ምስለ አግብርቲሁ
ዘእግዚአብሔር ሰቡሕ ክብር ወውዳሴ
በቤተ ባዕል ፈርዖን ብእሴ በዙኀ ድምሳሴ
እምተደለወ ነገደ ሌዋዊ ቴዎፍሎስ ሙሴ
እምዕደ ግብጻዊ እስመ ቤዘውከ እስራኤላዊ ሢመተ ነገደ ቤቱ ለአውሴ
ወሰድኮሙሂ ውስተ ድልው ማኅደርከ ቅዳሴ
ለደቂቀ ዮሴፍ ጥበባት ኤፍሬም ወምናሴ
አናግድኒ አሥመሩ ተወክፎተከ ብእሴ
ማዕደ አብርሃም ተዋሕዶ እንዘ ቅድሚሆሙ ለሥላሴ

<u>ሦስተኛ</u>

አመ ሐተታ ኢክህሉ ከመ ይግበርዋ ለምክረ አኪጦፌል ባዕድ ንጹሓነ
የማን ወጺጋም
ዓበይተ አቤሴሎም በነገር
ወአቤሴሎም ትሔይስ
ምክረ አረጋዊ ፤ ዘንጹሕ እምደም
እምክረ አኪጦፌል ቀዳማዊ
አምጣነ እኩት ይእቲ ምክረ አኪጦፌል ማኅምም
ዛቲሰ ምክረ ቃሉ ለቴዎፍሎስ ግሩም
ትበቁል ብዙኃነ ወትሔሉ ለዓለም
በዘንገብር ኩልነ ደቂቀ ሃይማኖት እም
ምክረ ቴዎፍሎስ ተዋሕዶ አምጣነ ሠናይት ወአዳም